# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

## ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ማውጫ ........................................ I
የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ) ........................................ I
(EXECUTIVE SUMMARY) ........................................ I
ክፍል አንድ ........................................ 1
መግቢያ ........................................ 1
የክትትል ኦዲቱ ዓላማ ........................................ 3
የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........................................ 3
የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ........................................ 4
ክፍል ሁለት ........................................ 5
የኦዲት ግኝቶች ........................................ 5
ኢንስቲትዩቱ ለስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና ጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍ መስጠትን በተመለከተ፡- ........................................ 5
በስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበር ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣በግንባታ፣ በተከላና ሙከራ ምርት ኢኒስቲትዩቱ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፡- ........................................ 11
በስጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍ የምርምር ስራ መከናወኑን እና ቴክኖሎጂዎች ተሰራጭተው መተግበራቸውን በተመለከተ፡- ........................................ 13
የስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ያካተተ ስለመሆኑ፡- ........................................ 16
የኢንስቲትዩቱ ንብረቶች/መሳሪያዎች እና ኬሚካሎች ለብክነት ሳይጋለጡ ስራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን በተመለከተ፡- ........................................ 18
ኢንስቲትዩቱ በስጋ፣ ወተትና መኖ ሎጀስቲክስ አመራርና ግብይት ዙሪያ ለማቀነባበሪያዎቹ ድጋፍ መስጠትን በተመለከተ፡- ........................................ 20
የስጋ፣ ወተትና መኖ ግብዓት አቅርቦት በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን መደረጉን በተመለከተ፡- ........................................ 24
ኢንስቲትዩቱ የስጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ፡- ........................................ 28
በስጋና ወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ተወዳዳሪ በመሆን ለአገር ውስጥና ለውጭ ሀገር በበቂ ሁኔታ ምርቶችን የሚያቀርቡ ስለመሆኑ፡- ........................................ 30

ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ የወተትና የመኖ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ማድረጉን በተመለከተ፡- ........................34
በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ዙሪያ ያሉ መልካም ተሞክሮዎች ተቀናብረው ተግባራዊ የተደረጉ ስለመሆኑ፡- ........................36
ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተደራጁና ለሚመለከተው አካል የተሰራጩ መሆኑን በተመለከተ፡- ........................38
ኢንስቲትዩቱ ሥጋና ወተት መዳረሻ ገበያ እስኪደርስ ድረስ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ለቄራዎች ግብረ መልስ በመስጠት አፈጻጸሙን ያሳደገ መሆኑን በተመለከተ፡-........................41
ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር ላይ ተሳትፈው ውጤት ያላስመዘገቡ ኢንዱስትሪዎችን በመለየት የኢንቨስትመንት ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረጉን በተመለከተ፡- ........................44
በኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ውጤታማነትን በተመለከተ፡- ........................45
በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎችን በመስክ በመከታተል የአፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ፡- ........................47
በኢንስቲትዩቱ የአማካሪ ምክር ቤት መቋቋሙን በተመለከተ፡- ........................49

ክፍል ሦስት ........................51

የመደምደሚያ ሀሳብ (CONCLUSION)........................51

3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው........................51
3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው ........................53

ክፍል አራት ........................63

የማሻሻያ ሀሳቦች (RECOMMENDATION) ........................63

## የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)

## (Executive summary)

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2007/2008 ዓ.ም በኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር አፈጻጸምን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች መኖራቸውን፤ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ያከናወነ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮቹ ካሉ ምክንያቱን በመለየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት በክትትል ኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው ፡-

- የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች ኢንስቲትዩቱ በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት በመስጠት ውጤት ማስመዝገብ አለመቻሉ፣
- ወተትና የወተት ውጤቶች የጥራት ደረጃ አጠባበቅ ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል ክትትል አለመድረጉ፣
- በመኖ ምርቶች ላይ የላብራቶሪ ትንተና እንዲደረግባቸው ኢንስቲትዩቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት አለመሥራቱ፣
- በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ በምርት ሂደት ባለሙያዎቹ ቀርበው እገዛ ያላደረጉ ሲሆን ባለሙያዎቹ ወደ ኢንዱስትሪዎቹ በሚሄዱበት ወቅት ስለ ምርት ሂደቱ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በጥያቄ ስለሚያባክኑ ማቀነባበሪያዎቹ ለኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ያላቸው ሙያዊ አመለካከት በመቀየሩ ሙያተኞቹን ለማስተናገድ አለመቻላቸው እና በምርት ዕቅድ ላይ አብሮ አለማቀድ እና የኢንስቲትዩቱ ድርሻ ምን እንደሆነ በዕቅዳቸው ላይ የማይገለጽ እና የማይታወቅ መሆኑ፣

- ከጥራት ጋር በተያያዘ የሥጋ እና ወተት ማቀነባበሪያዎች ያላቸው ላብራቶሪ ደረጃውን ያልጠበቀና ጥገና ያልተደረገላቸው እና በትክክል ስለመስራታቸው ማረጋገጫ (Calibration test) ያልተደረጉ መሆኑ፣ በቂ የላብራቶሪ ፋሲሊቲ (ይህም፡- የተለየ የላብራቶሪ ክፍል፣ ኤርኮንዲሽነር፣ ፋኖች እና ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች)፣ የላብራቶሪ ማስኬጃ መመሪያ ወይም ማንዋል የሌላቸው፣ የላብራቶሪ ቆሻሻ መቆጣጠሪያ(residue monitoring) መሳሪያ አለመኖር እና ኢንስቲትዩቱም ሞዴል ሰርቶ ማሳያዎች እና ላብራቶሪዎችን በማቋቋም በዚሁ መሰረት እንዲስፋፉ አለማድረጉ፣
- በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ኢንስቲትዩቱ በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ድጋፍ የማያደርግላቸው መሆኑ፣
- የሥጋ ኢንዱስትሪዎች የዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟላ ምርቶች ለሃገር ውስጥና ለአለም ገበያ በስፋት ማቅረብ አለመቻላቸው፤ የሥጋ ኢንዱስትሪዎች አፈጻጸም ከዓመት ዓመት እየቀነሰ የሚሄድበት ሁኔታ መስተዋሉ ለዘርፉ ስጋት መሆኑ፣
- ወተትና የወተት ውጤቶች ጥራትና ቁጥጥር እንዲሁም ደህንነት ማረጋገጫ ላይ ምርምር ማካሄድ አለመቻሉ፣ በፍየል ወተት ላይ ጥናት አለመደረጉና በኬሚካል ወተትን የማቆየቱ ሂደት ጠቀሜታውና ጉዳቱ ተለይቶ ለማቀነባበሪያዎቹ ሳይንሳዊ የሆነ ጥናት እንዲሰጣቸው አለመደረጉ፣
- የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ዕቅድ ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (ሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞችን...) ባካተተ መልኩ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት አፈጻጸሙን ያካተተ ሪፖርት ማግኘት አለመቻሉ፣
- በወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን በኤክስፖርትና ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባውን ወተት ለመተካት በሚያስችል (Import substitution) ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ እንዲችሉ አለመደረጉ፣

- የሀገራችን የወተት ማቀነባበሪያዎች በተወሰኑ አይነት (ፓስቸራይዝድ ወተት፣ እርጎ፣ አይብ፣ የገበታ ቅቤ እና የምግብ ቅቤ) ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን በሌሎች ክሬም፣ የተፈጨ ቺዝ፣ ፕሮቫለን ቺዝ፣ ሞዞሬላ ቺዝ፣ ፌታ ቺዝ፣ እስሞክድ ቺዝ፣ ፎንቲና ቺዝ ወ.ዘ.ተ ላይ ትኩረት እድርገው የማይሠሩ መሆኑ፣
- የማሽኒያ፣ የኬሚካል፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎች…፣ የቁም እንስሳት አቅርቦት በተለይ በሥጋና ወተት ፍላጎትና እንስሳት አቅርቦት ላይ የተወሰነ ደሰሳ ጥናት ቢከናወንም ህጋዊ በሆነ መልኩ አለመታተሙ እና ለማቀነባበሪያዎቹ አለመሰራጨቱና ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- በተጨማሪም የእንስሳት አቅርቦትን ችግር ለመፍታት የግል ባለሃብቶችና የቁራ ባለቤቶች መሬት ወስደው የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል እንዲያረቡ እና እንዲያደልቡ ብሎም ከይዞታቸው ለእርድ እንዲያቀርቡ የእንስሳት እርባታ (ራንች) እንዲያቋቁሙ አለመደረጉ፣
- ኢንስቲትዩቱ በሀገሪቱ የሚገኙትን የክልሎች የወተት ሃብት (Milk Shed)ና የመኖ የማምረት አቅም እንዲሁም የእንስሳት አቅርቦት መጠን በመለየት መረጃዎችን ማደራጀት አለመቻሉ፣
- የእንስሳት ዱካን (Tracibility) ለመመዝገብ የሚያስችል መዝገብ (records) ተግባራዊ እንዲደረግ በማድረግ ከግበርነ ሚ/ር ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን በማጎልበት የእንስሳት ጤና ሥርዓትና ቁጥጥርን አስመልክቶ መረጃዎችን ለተቀባይ ሀገራት የማድረስና የማስተዋወቅ ሥራ አለመከናወኑ፣

## ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት በማገልገል፣ የውጪ ምንዛሬ በማስገኘት እና የውጪ ምርቶችን በመተካት ረገድ ከፍተኛ ሀገራዊ ጠቀሜታ እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን ከእንስሳት ሀብታችን ተገቢውን ጠቀሜታ ለማግኘትና ምርትና ምርታማነትን በአግባቡ ማሳደግ እንዳይቻል እንቅፋት የሆኑት ዋነኛ ምክንያቶች ውስጥ ባህላዊ የእንስሳት አረባብ ዘዴ፣ የመኖ በብዛትና በጥራት ያለመኖር፣ በቂ የእንስሳት ጤና አገልግሎት አለመሟላት እና ዘመናዊ የግብይት ስርዓት አለመኖር ናቸው፡፡
2. ከእንስሳት ሀብታችን የተሻለ ምርትና ገቢ ለማግኘት እንዲቻል በህብረተሰቡ ዘንድ የተጠናከሩ ጥረቶች በመደረግ ላይ ሲሆኑ መንግስትም በሥጋና ወተት ምርትና አቅርቦት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላትን አቅም ለመገንባት እና የሥጋና የወተት ምርትና አቅርቦት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 143/2000 ዓ.ም በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሥር አቋቋመ፡፡ በ2002 ዓ.ም ኢንስቲትዩቱ በሥጋና ወተት ማምረት፣ አቅርቦት፣ ማቀነባበር እና ግብይት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላትን አቅም ለመገንባት፣ የሥጋና የወተት ምርትና አቅርቦት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል፣ በመስኩ ባለሃብቶች እንዲሳተፉ በማበረታታት ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን የሚያሟላ እንስሳትና የእንስሳት ምርቶች ለውጭና ለአገር ውስጥ ገበያ በአይነትና በብዛት የሚቀርብበትን ሁኔታ ማመቻቸት ለማስቻል ተጠሪነቱ ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሆኖ በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 176/2002 በማሻሻያ ተቋቁሟል፡፡ ይህ ዘርፍ እንዲጠናከርና የግል ባለሃብቱም በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር በማስፋፋት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶችን ማቅረብ እንዲቻል የአቅም ግንባታ፣ የገበያ ማስፋፋትና የኢንቨስትመንት ድጋፎችን ለባለሃብቱ እንዲሰጥ ለማድረግ የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ተጠሪነቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሆኖ በደንብ ቁጥር 295/2005 ዓ.ም በድጋሚ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ደንብ ውስጥ ኢንስቲትዩቱን የሚያማክር የአማካሪ ምክር ቤት እንዲመሰረትና ምክር

ቤቱም ሰብሳቢና አግባብ ካላቸው የመንግሥት መ/ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ ጭምር የተውጣጡ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት እንዲኖሩትና እንዲቋቋም በአንቀጽ 8/1 ተፈቅዶለታል፡፡

3. አገራችን ከፍተኛ የእንስሳት ሃብት ያላት ስትሆን 53.4 ሚሊዮን የቀንድ ከብት፣ 25 ሚሊዮን በጎች፣ 22.78 ሚሊዮን ፍየሎች እና 49.3 ሚሊዮን ድሮዎች እንዲሁም 4.9 ሚሊዮን የባህላዊ፣ 41,687 የሽግግርና 144,258 የዘመናዊ ቀፎዎች እንዳላት በCSA (Central Statistics Authority), 2010/2011 እ.ኤ.አ መረጃ ያስረዳል፡፡ ነገር ግን ከዚህ የእንስሳት ሃብት የሚገኘው ምርትና ምርታማነትም በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ሃገሪቱ 10.7 ሚሊዮን የወተት ላሞችና 7.4 ታላቢ ላሞች ሲኖራት 4.06 ቢሊዮን ሊትር ወተት እንዲሁም 49.3 ሚሊዮን ድሮዎች 98.3 ሚሊዮን እንቁላልና 60 ሺህ ቶን ሥጋ የተመረተ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም በ5.13 ሚሊዮን ቀፎዎች ውስጥ ከሚገኙ 10 ሚሊዮን ህብረ ንቦች 53.86 ሚሊዮን ኪ.ግ ማር ሲገኝ በሃገራችን ውስጥ ከሚገኙ የውሃ አካላት ማለትም ከግድቦች፣ ሃይቆችና ኩሬዎች በዓመት ከ15,417-17,308 ቶን የዓሳ ሥጋ እንደተመረተ በዚሁ ዓመት የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡

4. ከእንስሳት የሚገኘው ምርትና ምርታማነት አናሳ ከመሆኑ የተነሳ የሃገራችን የነፍስ ወከፍ ፍጆታ ዝቅተኛ ነው፡፡ በአፍሪካ ሀገሮች የዳልጋ ከብት ሥጋ ፍጆታ 23 ኪ.ግ፣ የወተት ፍጆታ 27.5 ሊትር፣ ሲሆን የኛ አገር የዳልጋ ከብት ስጋ ፍጆታ 9 ኪ.ግ፣ የወተት 19 ኪ.ግ፣ የእንቁላል 1.2፣ የዶሮ ሥጋ 1ኪ.ግ፣ የዳልጋ ከብት ሥጋ ምርታማነት (Dressing percentage) ከ35-40 % ነው፡፡ ከበግና ፍየል የሚገኘው አማካይ የሥጋ ምርት መጠን በቅደም ተከተል ሲቀመጥ 10 እና 9 ኪ.ግ ሲሆን የመስራቅ አፍሪካ አገሮች ግን ከበግ በአማካይ 13.5 ኪሎ ግራም ከፍየል 13.1 ኪሎ ግራም ሥጋ ያገኛሉ፡፡

5. በመሆኑም ይህ የእንስሳት እና የእንስሳት ተዋጽኦ ዘርፍን ውጤታማ ለማድረግ ጉልህ ሚና ያለው የስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መንግስት የሰጠውን ተግባርና ኃላፊነትን በተቀላጠፈ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ መሆኑን በማጣራት በአሰራር ሂደት የተገኙ ክፍተቶችን የመለየት ሰራ ተሰርቶ ነበር፤ ስለሆነም በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፤

## የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

6. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2007/2008 ዓ.ም በኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር አፈጻጸምን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን፣ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ያከናወነ መሆኑን የክትትል ኦዲት በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮቹ እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

7. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው ከ2009 - 2010 ዓ.ም ያሉትን የሁለት በጀት ዓመት የሥራ ክንውኖችን እንቅስቃሴ መሰረት ባደረገ በኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር አፈጻጸምን በተመለከተ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን እና ኢንስቲትዩቱ እነዚህን የኦዲት ግኝቶች የሚፈታበት የኦዲት ግኝት ማሻሻያ ሃሳቦች የሚተገበሩበትን የማሻሻያ እርምጃ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ባቀረበው መሰረት የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች በተዘጋጀው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት መተግበራቸውን እና ችግሮቹ መቀረፋቸውን ለማረጋገጥ የክትትል ኦዲቱ እስከተከናወነበት እስከ 2010 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በኢንስቲትዩቱ የተከናወኑ ስራዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

8. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በኢንስቲትዩቱ እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ አራት የሥጋ (ሃሽም/ሂልሜክስ፣ ሉና እና ኤልፎራ/ደብረ ዘይት/ ኤክስፖርት ቄራዎች) እና ሶስት የወተት ማቀነባበሪያ (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ እና ጀኔሲስ ፋርም) እና ሁለት የመኖ ማቀነባበሪያዎች (አለማ ካዋዳይስ እና አዲስ አለም ሞጆ) የክትትል ኦዲት ቡድኑ በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው

ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለክትትል ኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ነው፡፡

**<u>የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች</u>**

9. የክትትል ኦዲቱን ለማከናወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች እና ኢንስቲትዩቱ በኦዲት ግኝቱ ላይ እርምጃ ለመውሰድ ያዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

**ኢንስቲትዩቱ ለስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና ጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍ መስጠትን በተመለከተ፡-**

10. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

11. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች በምርት ዕቅድ፣ በምርት ሂደት እና በምርት ጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት በመስጠት ውጤት ማስመዝገብ አለመቻሉ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሥጋ ማቀነባበሪያዎች (ሃሽም/ሂልሚክስ፣ ኤልፎራ እና ሉና ቄራዎች)፣ የወተት ማቀነባበሪያዎች (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ጄኔሲስ ፋርም፣ ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) እና የመኖ ማቀነባበሪያዎች (አዲስ አለም ሞጆ እና አለማ ካዋዳይስ) በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ እና በኢንስቲትዩቱ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ተገኝቶ ነበር፡፡

12. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች በምርት ዕቅድ፣ በምርት ሂደት እና በምርት ጥራት ቁጥጥር በማድረግ ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ እንዲሁም የዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟላ ምርት ለሃገር ውስጥና ለዓለም ገበያ እንዲያቀርቡ መደገፍ አለበት የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

13. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር የተለያዩ የስጋ፣ የወተትና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች የጋራ ዕቅድ እንዲያወጡ በማድረግ በአፈጻጸም ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በቅርበት ተከታትሎ ለመፍታት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

14. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

15. ኢንስቲትዩቱ በወተት የምርት ዕቅድና የምርት ሂደት እንዲሁም የምርት ጥራት ቁጥጥር ላይ ለወተት ማቀነባበሪያዎች ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠቱን

በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

- ኢንስቲትዩቱ በወተት ምርት ላይ የመጀመሪያ ደረጃ፣ ኬሚካላዊና ማይክሮባዮሎጂካዊ የጥራት ፍተሻ አድርጎ እንደማያውቅ የጄኔሲስ ፋርም የስራ ሀላፊዎች የገለፁ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ በ2010 ዓ.ም ከተወሰኑ የወተት ማቀነባበሪያዎች ምርት ላይ 860 ናሙና ወስዶ ኬሚካላዊ እና ማይክሮባዮሎጂካል ፍተሻ እንዳደረገ ቢገለፅም ከሁሉም የወተት ማቀነባበሪያዎች ናሙና መውሰድ እና ፍተሻ ማድረግ እንዳልተቻለ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ የገለፁ መሆኑ፣ ይሁን እንጂ ናሙና ተወስዶ ፍተሻ የተደረገበትና ውጤቱ ተተንትኖ ለማቀነባበሪያዎቹ የተሰራጨበት/የደረሰበት ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ አለመቅረቡ፤

- የጄኔሲስ ፋርም በወተት ምርቱ ውስጥ አፍላቶክሲን የተባለው ንጥረ ነገር ከአስገዳጅ ብሔራዊ የወተትና የወተት ተዋጽኦ የአፍላቶክሲን/afelatoxin/ መጠን በላይ በመገኘቱ ምክንያት በሚል ለአንድ አመት የወተት ማቀነባበር ስራ እንዳይሰራ በኢትዮጵያ የምግብ፣ መድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በደብዳቤ ያገደው ቢሆንም ማቀነባበሪያው አስገዳጅ ብሔራዊ የወተትና የወተት ተዋጽኦ የአፍላቶክሲን/afelatoxin/ መጠንን ያሟላ መሆኑ በኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅትና ብሌስ አግሮ ላብራቶሪ ኃ.የጠ.የግ.ኩባንያ ተረጋግጧል(ወተቱ ከአፍላቶክሲን ንጥረ ነገር ነፃ መሆኑ) የማቀነባበሪያው የስራ ሀላፊዎች የገለፁ መሆኑና ከቀረቡት ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፣

- ኢንስቲትዩቱ የወተት ማቀነባበሪያዎች የወተት ማሰባሰቢያና ማቀዝቀዣ ማዕከል እንዲያቋቁሙ እንዲሁም የተለየ ንጽህናውን የጠበቀ የወተት መረከቢያና መሸጫ ቦታ እንዲኖራቸው በተጨባጭ ሁኔታ ድጋፍ እንዳላደረገ ከኢንስቲትዩቱ እና በመስክ ከታዩ የወተት ማቀነባበሪያ የሥራ ሃላፊዎች ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

- ከ2009-2010 በጀት ዓመት ጄኔሲስ ፋርም፣ አደአ፣ ሾላና ሆላንድ ዴይሪ የወተት ማቀነባበሪያዎች ማሟላት የሚገባቸውን ስታንዳርድ ባለማሟላታቸው እንዲሁም ጄኔሲስ ፋርምና ኤሌምቱ ወተት ማቀነባበሪያዎች ደግሞ በወተት ጥራት ጉድለት ምክንያት /በአፍላቶክሲን ችግር/ የተነሳ ከገበያ ታግደው እንደነበር ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣
- በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ የወተት አፍላቶክሲን ምርመራ አድርጎ እንደማያውቅና መፈተሻ መሳሪያውም እንደሌለው እና የኢንስቲትዩቱ ላብራቶሪም 40 ዓመት ያስቆጠረና ከዘመኑ ጋር አብሮ የማይሄድ መሆኑ፣
- ወተት አቅራቢዎች ለወተት ባልተዘጋጀ እቃ እንደሚያቀርቡ በኦዲቱ ወቅት የታዩ የወተት ማቀነባበሪያዎች የስራ ሀላፊዎች የገለፁ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ወተትና የወተት ውጤቶች የጥራት ደረጃ አጠባበቅ ህግ፣ ደንብና መመሪያ እንደሌለው የኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ መሆኑ፣

16. ኢንስቲትዩቱ በስጋ የምርት ዕቅድና የምርት ሂደት እንዲሁም የምርት ጥራት ቁጥጥር ላይ ለስጋ ማቀነባበሪያዎች ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠቱን በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

    - በሳውዲ አረቢያ ኢንስፔክሽን ቡድን አስተያየት መሰረት ከአለም አቀፍ የምግብ ደህንነት ደረጃዎች ጋር በተያያዘ ምክንያት የተወሰኑ ቄራዎች /ሀሽም፣ አልነጃም እና አበርገሌ/ ከሳውዲ አረቢያ ገበያ መታገዳቸውን የኢንስቲትዩቱ የ2010 በጀት ዓመት የድጋፍ ስራዎች እቅድ በተከለሰበት ወቅት ለመረዳት የተቻለ መሆኑ፣
    - ለእርድ የሚመጡ እንስሳት ከተሰበሰቡበት አካባቢ ተነስተው ከአንድ ቀን እስከ ሰባት ቀን ድረስ እንደሚጓዙ፣ ይህም በእንስሳው ምርት ላይ የጥራት ችግር እንደሚያመጣ በኦዲቱ ወቅት የታዩ የስጋ ማቀነባበሪያ የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ ከስጋ ማቀነባበሪያዎቹ ጋር የመግባቢያ ሰነድ እንደሚፈራረሙ ነገር ግን የጋራ እቅድ ከማቀነባበሪያዎቹ ጋር እንደማያቅዱ፣

- ኢንስቲትዩቱ ለስጋ ማቀነባበሪያዎች ጥራቱን የጠበቀ ስጋ መዳረሻ እስኪደርስ ድረስ በሰንሰለቱ ውስጥ ክትትል እንደማያደርግ በኦዲቱ ወቅት ከታዩ የስጋ ማቀነባበሪያ የስራ ሀላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ ጥራቱን የጠበቀ ስጋ ከማቀነባበሪያው እስከ ኤርፖርት አካባቢ እስኪደርስ ድረስ ክትትል እንደሚያደርጉ፤ ነገር ግን ከኤርፖርት በኋላ እስከ መዳረሻ ገበያ ያለውን ሂደት እንደማይከታተሉ በመሆኑም በ2008 ዓ.ም መጨረሻ ክረምት ላይ በሉና፣ ሞጆ ሞደርንና ኦርጋኒክ ኤክስፖርት ቄራዎች ወደ ዱባይ የተላከ ስጋ ተበላሽቶ/በጥራት ምክንያት የተቃጠለበት ሁኔታና ከገበያም እንደታገዱ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ መሆኑ፣

- ሀሽም፣ አልነጃምና አበርገሌ ኤክስፖርት ቄራዎች አስፈላጊውን ስታንዳርድ ባለማሟላታቸው ከነሀሴ 2009 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ውጭ ስጋ ከመላክ መታገዳቸውን እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የስጋ ላብራቶሪ ክፍል ባለመኖሩ ለሶስት ኤክስፖርት ቄራዎች /ኦርጋኒክ፣ ሉና እና አክሽከር/ የናሙና ፍተሻ ለማድረግ ከ80,000 ብር በላይ ወጪ እንዳወጣ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ ለስጋ ማቀነባበሪያዎች በቅድመ ምርት፣ በምርት ሂደትና ድህረ ምርት ሳኒቴሽንና ሀይጂን ላይ በተግባር ላይ የተመሰረተ ድጋፍ እንደማያደርግ በኦዲቱ ወቅት ከታዩ የስጋ ማቀነባበሪያ የስራ ሀላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

17. ኢንስቲትዩቱ በመኖ የምርት ዕቅድና የምርት ሂደት እንዲሁም የምርት ጥራት ቁጥጥር ላይ ለመኖ ማቀነባበሪያዎች ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠቱን በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

- ኢንስቲትዩቱ የመኖ ላብራቶሪ እንደሌለው እና ከ2009-2010 ዓ.ም በመኖ ምርቶች ላይ የላብራቶሪ ትንተና እንዲደረግባቸው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እንዳልሰራ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተጠየቁ የመኖ ማቀነባበሪያ የሥራ ሃላፊዎች ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት አድርጎላቸው እንደማያውቅ የመኖ ማቀነባበሪያ የስራ ሀላፊዎች የገለፁ ሲሆን፣

- ኢንስቲትዩቱ ለመኖ ማቀነባበሪያዎች በምርት እቅድ፣ በምርት ሂደት እና በጥራት ቁጥጥር ላይ በተግባር የተደገፈ ድጋፍና የማማከር አግልግሎት እንዳልሰጡ ነገር ግን ምክረ ሀሳብ እንደሚሰጡ ከኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለማሳያ፡- ለመኖ ዳይሬክቶሬት 6 የሰው ሀይል የተፈቀደ ቢሆንም 1 ባለሙያ ብቻ እንዳለና ይህም ባለሙያ የትምህርት እድል እንዳገኘና መደቡ ባዶ የሰው ሀይል እንደሚኖረው እና ለዘርፉም ትኩረት ተሰጥቶ እንዳልተሰራ ለማወቅ ተችሏል፡፡

18. በአጠቃላይ ከጥራት ጋር በተያያዘ በኦዲቱ ወቅት የታዩ የስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎች ላብራቶሪ ክፍል እንዳላቸው፣ ነገር ግን ያረጁና ጥገና ያልተደረገላቸው እና በትክክል ስለመስራታቸው ማረጋገጫ (Calibration test) የሌላቸው መሆኑ፣ በቂ የላብራቶሪ ፋሲሊቲ (ይህም፡- የተለየ የላብራቶሪ ክፍል፣ ኤር ኮንዲሽነር፣ ፋኖች እና ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች)፣ የላብራቶሪ ማስኬጃ መመሪያ ወይም ማንዋል የሌላቸው፣ የላብራቶሪ ቆሻሻ መቆጣጠሪያ (residue monitoring) መሳሪያ የሌላቸው ከመሆኑ በተጨማሪ፤

19. ላብራቶሪዎቹ የኬሚካል እና ሪኤጀንት እጥረት ያለባቸው መሆኑን እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ ሞዴል ሰርቶ ማሳያዎች እና ላብራቶሪዎችን በማቋቋም በዚሁ መሰረት እንዲስፋፉ አለማድረጉን ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከቀረበላችው ቃለ መጠይቅ እና የኦዲት ቡድኑ ባደረገው የመስክ ምልከታ ታውቋል፡፡

20. የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች በምርት ሂደት ላይ በተግባር ላይ የተደገፈ ክህሎት እንደሌላቸው እና  በምርት ዕቅድ ላይ ኢንስቲትዩቱ እንደማይሳተፍ በክትትል ኦዲቱ ወቅት የስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

21. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ካለው የአቅም ውስንነትና የላብራቶሪ እጥረት የተነሳ ለዘርፉ ፋብሪካዎች በምርት ሂደት፣ ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍ ለማድረግ አስቸጋሪ መሆኑን እና ኢንስቲትዩቱ እዚህ ደረጃ ያልደረሰ መሆኑንና ወደ ፊት በቁርኝት ፕሮግራም አቅም ተገንብቶ የሚሰራ እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡

22. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ፡-

- የወተት ጥራት መፈተሻ ላቦራቶሪዎች ከነባለሙያ ያላቸው አንዳንድ የወተት ፋብሪካዎች ብቻ መሆናቸው፤ እያንዳንዱ ፋብሪካ ኬሚካላዊና ማይክሮባዮሎጂያዊ በራሱ ላቦራቶሪ ፍተሻ ማድረግ ግዴታው እንደሆነ እና በተቻለ መጠን ደግሞ በየሶስት ወሩ አንድ ጊዜ ከማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ናሙና ተወስዶ በኢንስቲትዩቱ የጥራት ፍተሻ እንደሚደረግ፤ ነገር ግን የናሙናው ግብረ-መልስ በይበልጥ የሚሰጠው ምርቱ የጥራት ችግር ካለው ብቻ እንደሆንና ጤናማ ከሆነ ግብረ-መልስ ላይሰጥ እንደሚችል፤
- ወተት አቅራቢዎች ወተት የሚሰበስቡት ከገበሬው ሲሆን ገበሬዎች ምርታቸውን በአካባቢው ባለው እቃ እንደሚያቀርቡ፣ የወተት ማቀነባበሪያ እቃን ለማዘመን በአንድ የውጪ ድርጅት ድጋፍ አንድ ማሽን ተተክሎ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለወተት አቅራቢዎች ማሰራጨት መጀመሩ ነገር ግን ከሀገሪቱ ሥፋት አንፃር የወተት ማቅረቢያ እቃውን በአንድ ጊዜ ማዳረስ ባይቻልም በሂደት እየተቀረፈ ይመጣል የሚል እምነት እንዳለ፤
- የወተት ግብይትን በህግ ማዕቀፍ እንዲደገፍ ለማድረግ ለአማካሪ ድርጅት ተሰጥቶ ጥናቱ እየተካሄደ መሆኑና ጥናቱ እንዳለቀ ለፓርላማ ቀርቦ የሚፀድቅ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

**በስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበር ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና ሙከራ ምርት ኢንስቲትዩቱ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፡-**

23. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

24. በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ኢንስቲትዩቱ በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ላይ ድጋፍ ያላደረገላቸው መሆኑ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ ከታዩ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች ከተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ እና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ተገኝቶ ነበር፡፡

25. ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበር ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና ሙከራ ምርት ድጋፍ ማድረግ አለበት የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

26. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ኢንስቲትዩቱ በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ላይ ድጋፍን ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

27. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

28. ኢንስቲትዩቱ ለስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና ሙከራ ምርት ዙሪያ ድጋፍ አድርጎላቸው እንደማያውቅ በኦዲቱ ወቅት የታዩ የስጋ፣ የወተትና የመኖ ማቀነባበሪያዎች የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

29. በሉና ኤክስፖርት ቄራ፣ ኤልፎራ ኤክስፖርት ቄራና ጀኔሲስ ፋርም ማቀነባበሪያዎች ከውጭ ሃገር የገቡ የማቀነባበሪያ ማቀዝቀዣ መሳሪያዎች ያላቸው ቢሆንም ከውጭ እስኪገባ ካለው ሂደት በስተቀር ከገባ በኋላ በኢንስቲትዩቱ በኩል የተደረገ ድጋፍ አለመኖሩ እንዲሁም በሆላንድ ዴይሪና

ሁለት የሱዳን ቄራዎች በቴክኖሎጂ መረጣ እና በተከላ ላይ የኢንስቲትዩቱ ተሳትፎ አለመኖሩ ለድርጅቶቹ ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ምላሽ ታውቋል፡፡

30. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ኢንስቲትዩቱ አጠቃላይ የአቅም ውስንነት ስላለው ለስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና ሙከራ ምርት ዙሪያ ድጋፍ ማድረግ አለመቻሉና ይህ ገና ወደ ፊት በቁርኝት ፕሮግራም አቅም ተገንብቶ የሚሰራ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመለትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተጠቀሱትን እና ሌሎች መሰል ተግባራትን ሊደግፋቸዉ ለተቋቋመበት ኢንዱስትሪዎች መስጠት ግዴታዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንስቲትዩቱ አንድም በሀገሪቷ ዉስጥ የትኛዉም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በእንስሳት ዉጤቶች ኢንዱስትሪ ላይ የሚያስተምሩት እና የሚያስመርቁት የሰዉ ኃይል አለመኖራቸዉ ከፍተኛ ችግር ሲሆን በራሳቸዉ ጥረት እና በዉጪ ሀገር ተምረዉ ልምድ ያላቸዉን ባለሙያዎች ከሀገር ዉስጥ ገበያ ላይ አግኝቶ ቀጥሮ ለማስራት ደግሞ የተቋሙ መዋቅር ሳቢ ካለመሆኑ የተነሳ የተቋቋመለትን ዓላማ ሊፈፅም የሚችል የሰዉ ኃይል እንደሌለው ገልፀዋል፡፡
- ነገር ግን ከተጠቀሱት ግኝቶች ዉስጥ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን በግንባታ ወቅት የሚያማክሩ ባለሙያዎችን በመቅጠር ድጋፍ እየተደረገ እንደሚገኝ፤ ልምድ ያላቸዉን የኢንጂነሪንግ ባለሙያዎችንም ቢሆንም የሚስብ መዋቅር ባለመኖሩ በግንባታ ላይ የሚሰጠዉ ድጋፍ በአንድ ባለሙያ ብቻ ስለሆነ ተደራሽነቱም በዚያዉ ልክ ዉስን መሆኑ፤ በማሽነሪ ተካላ እና የምርት ሙከራ በሚመለከት የወተት ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች የየትኛውን ሀገር ምርት ቢያስገቡ ጥራት እንዳለው በሚጠየቁበት ጊዜ ምክር እንደሚሰጡ፤
- ሁለት የሱዳን ቄራዎችን በተመለከተ፡ ሲገነቡ እና ፈቃድ ሲሰጣቸው በኢንስቲትዩቱ ዕውቅና ስላልነበረ እና በግንባታ ሂደት ላይ እያሉ ኢንስቲትዩቱ በራሱ መንገድ እንደደረሰባቸው እና ተቀራርበው ስለተሰሩ የተወሰኑ የማስተካከያ ሃሳቦች ተሰጥቷል ከዚያም በኃላ ግብርና ሚኒስቴር ዕውቅና ስለሰጣቸው የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡

31. ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ ይህንን ተግባር ማከናወን የሚችል የሰው ኃይል በማብቃት እና ከግብርና ምርምርና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መሥራት ስለሚጠበቅበት ምክንያቱ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

***በስጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍ የምርምር ስራ መከናወኑን እና ቴክኖሎጂዎች ተሰራጭተው <u>መተግበራቸውን በተመለከተ፡-</u>***

32. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

33. ኢንስቲትዩቱ ከ2005-2008 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት ሊለሙ የሚችሉ ወጪ ቆጣቢ፣ ምርትና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ እና የምርት ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች አለመሸጋገሩ፣ ኢንዱስትሪዎቹም የራሳቸውን የምርምርና ሥርጸት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ ሊደግፍ አለመቻሉ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች እና ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ተገኝቶ ነበር፡፡

34. ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት፣ ኢንዱስትሪዎቹ የምርምርና ሥርጸት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ በማድረግ እና የውጭ ባለሃብቶች በዘርፉ እንዲሳተፉ በማድረግ ወጪ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ኢንዱስትሪዎች ሊያሸጋግር እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

35. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት ሊለሙ የሚችሉ ወጪ ቆጣቢ፣ ምርትና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ እና የምርት ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች ለማሸጋገር ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

36. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

37. ኢንስቲትዩቱ ለስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎች ከፍተኛ ችግር ሆኖ የሚታየውን የመብራት መቆራረጥ በተወሰነ ደረጃ ማቃለል የሚያስችል የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ እና ውሃን መልሶ አጣርቶ መጠቀም የሚያስችል ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ እገዛ እንዳላደረገላቸው በክትትል ኦዲቱ ወቅት የስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

38. የአደአ የህብረት ስራ ማህበር የወተት ማቀነባበሪያ በመብራት መቆራረጥ ምክንያት አንድ የውሀ ፓምፕ፣ ስድስት ኮምፕሬሰር ማሽኖች በብር እስከ 300,000 ድረስ ጉዳት እንደደረሰባቸው ከማቀነባበሪያው የስራ ሀላፊዎች በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

39. ኤክስፖርት ቄራዎች ስጋን በተቆራረጠ መልኩ የሚልኩበትን የቅንብር ስርዓት እንዳልጀመሩ እንዲሁም ለኤክስፖርት የሚጠቀሙት የቆላ ስጋን ብቻ እንደሆነና ለዚህም ጉዳይ በኢንስቲትዩቱ በምርምር መፍትሄ እንዳልተሰጠው በክትትል ኦዲቱ ወቅት የተጠየቁ የስጋ ማቀነባበሪያ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

40. ኢንስቲትዩቱ ለቄራዎቹ ጠንካራ ስጋን ማለስለስ የሚያስችል ቴክኖሎጂ በመቀመር/በመፍጠር እንዲተገብሩት አለማድረጉ፣ እንዲሁም ወተትና የወተት ውጤቶች ጥራትና ቁጥጥር እንዲሁም ደህንነት ማረጋገጫ ላይ ምርምር እንዳላደረገና ለኢንዱስትሪዎች እንዳልደረሳቸው በኦዲቱ ወቅት የታዩ ከቄራ ድርጅቶችና ወተት ማቀነባበሪያዎች የስራ ሀላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

41. ወተትና የወተት ውጤቶች ጥራትና ቁጥጥር እንዲሁም ደህንነት ማረጋገጫ ላይ ምርምር እንዳላደረገ በኦዲቱ ወቅት የታዩ ከወተት ማቀነባበሪያዎች የስራ ሀላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. በክትትል ኦዲቱ የታዩ የስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎች የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች የተሸፈኑ (Safety Tanak) እንደሌላቸው የኦዲት ቡድኑ ባደረገው ምልከታ ለመመልከት ችሏል፡፡

43. ኢንስቲትዩቱ ከ2009-2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት ሊለሙ የሚችሉ ወጪ ቆጣቢ፣ ምርትና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ እና የምርት ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ

ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች አለመሸጋገሩ፤ እንዲሁም ኢንዱስትሪዎቹም የራሳቸውን የምርምርና ሥርጸት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ ሊደግፍ አለመቻሉ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች እና ቃለ መጠይቅ ታውቋል፡፡

44. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት ሊለሙ የሚችሉ ወጪ ቆጣቢ፣ ምርትና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ እና የምርት ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች ከማሸጋገር አንፃር የተከናወኑ ውስን የምርምር ስራዎች እንዳሉ ነገር ግን ወደ ኢንዱስትሪዎች እንዳልተሰራጩና ኢንዱስትሪዎቹም የራሳቸው የምርምር ተቋም እንዲያቋቁሙ አለመደረጉን የገለፁ ሲሆን፣ ይህን ለማድረግ ኢንስቲትዩቱ ትልቅ የአቅም ክፍተት እንዳለበትና ኢንስቲትዩቱ የራሱ የምርምር ማዕከል የሌለው በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

45. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ፡-

- ኢንዱስትሪዎች የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂዎች እንዲጠቀሙ፤ ፋሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻዎችን በማከም መልሰዉ ለአገልግሎት እንዲያዉሉ ኢንስቲትዩቱ ሊያደርግ የሚችለዉ ከእያዳንዱ ፋብሪካዎች የሚወጡ ቆሻሻዎችን እንደየ ባህሪያቸዉ ምን ያህል ኃይል ብክነትና ብክለት እንደሚያስከትሉ እንዲሁም ቆሻሻን በአግባቡ ሥራ ላይ ከዋሉ ደግሞ ምንያህል ኃይል ማመንጨት እንደሚችሉ የማማከር አገልግሎት መስጠት ሲሆን ይህ ተግባር በባለሙያ እጥረት በሁሉም ፋብሪካዎች ተደርጓል ባይባልም በተመረጡት ግን ተጨባጭ ሥራ እንደተሰራ ለአብነትም በቢሾፍቱ ከተማ የሚገኘዉ ኤልፎራ አግሮ-ኢንዱስትሪ (የዶሮ) ለአካባቢዉ ማህበረሰብ ከፍተኛ ስጋት የነበረ የቆሻሻ አወጋገድ እንዲያስተካክል ተደርጓል፤ በኦርጋኒክ ኤክስፖርት ቄራም በተመሳሳይ፤ በአጠቃላይ ፋብሪካዎች ባዮጋዝ በሚያመነጩት የኤሌክትሪክ ኃይል ማሽኖችን ምን ያህል ሊያንቀሳቅስ ይችላል የሚለዉ እንደተጠበቀ ሆነ የኤሌክትሪክ ችግር እንደ ሀገር ትኩረት የሚፈልግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

- ሥጋን በተቆራረጠ መልኩ ለማምረት በተግባር የመስራት ብቃትን (ክህሎት) የሚፈልግ መሆኑና ኢንስቲትዩቱ ይህንን ድጋፍ ለመስጠት የአቅም ዉስንነት መኖሩ ነገር ግን በኤክስፖርት ቄራዎች የሚገኙ ሰራተኞች ይህንን ክህሎት እንዲያገኙ ባለሙያዎችን ከውጭ ሃገር በማስመጣት በተደጋጋሚ ስልጠና እንደተሰጠ፤ የደጋ እንስሳት ለኤክስፖርት አገልግሎት አለመዋልን በሚመለከት ማንኛዉም የኤክስፖርት ንግድ የሚወሰነዉ በደንበኞች ፍላጎት ላይ መሆኑ፤ አሁን ያሉን የሥጋ ደንበኞች በአብዛኘዉ የሚፈልጉት ከሀገሪቷ ቆላማ አካባቢ በሚመጡ እንስሳት የታረደዉን ሥጋ ስለሆነ አማራጭ ደንበኛ/መዳረሻ ገበያ እስካልተፈጠር ድረስ በዚሁ መቀጠሉ የማይቀር መሆኑ፤ የደጋዉ እንስሳት ሥጋቸዉ በፍሪጅ ዉስጥ ለረጅም ጊዜ ስለማይቆይ አሁን ያሉን ደንበኞች አልፈለጉትም በዚህ ላይ ምርምር ቢሰራም ሊገኘው የሚችለዉ ዉጤት ወይ የእንስሳት አመጋገቢ ስርዓትን መቀየር አልያም የሚኖሩበትን አካባቢ መቀየር ከባሰ ደግሞ ሥጋዉ ሳይበላሽ ረጅም ቀናት እንዲቆይ ሌላ ባእድ ነግር (preservative methods) መጠቀም (በደንበኞች የማይመረጥ) እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

46. የኢንስቲተዩቱ የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የማማከሩ ጉዳይ ባለሙያ በመሟላት ሁሉም ፋብሪካዎች ላይ ተደራሽ ማድረግ፤ የኤሌክትሪክ ችግር የሀገር ችግር ቢሆንም ግን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መሰራት ስላለበት እና ከውጪ ባለሙያ በማስመጣት ስልጠና እንደተሰጠ ቢገለፅም የስልጠናው ውጤት ኤክስፖርት ቄራዎች ስጋን በተቆራረጠ መልኩ የሚልኩበትን የቅንብር ስርዓት መዘርጋት ስላልቻለ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡

**የስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ያካተተ ስለመሆኑ፡-**

47. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

48. የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ዕቅድ ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (ሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞችን) ባካተተ መልኩ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት አፈጻጸሙን ያካተተ ሪፖርት በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ማቅረብ አለመቻሉ፤

49. ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት የሥርዓተ ጾታ ዘርፍን ለማካተት የሚያስችለው የስርዓተ ጾታ ጉዳይ ባለሙያን በእያንዳንዱ ዕቅድ እንዲሳተፍ የማያደርግ መሆኑን እና የስርዓተ ጾታ ጉዳይን የሚከታተለው በአንድ ባለሙያ (Focal Person) ብቻ በመሆኑ ውጤታማ መሆን አለመቻሉ በኦዲቱ ወቅት ከኢንስቲትዩቱ የስራ ሀላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ የታወቀ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

50. በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፉ በተለይም ለሴቶችና ወጣቶች የሥራ እድል እንዲፈጠር ብሎም ሀገሪቷን በዘርፉ ተወዳዳሪ ማድረግ እንዲቻል የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (Cross Cutting Issues) ያካተቱ ሊሆን ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

51. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ዕቅድ ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞችን) ባካተተ መልኩ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት አፈጻጸሙን ያካተተ ሪፖርት ለማዘጋጀት ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

52. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

53. ኢንስቲትዩቱ የስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል አንድ የሰርዓተ ጾታ ጉዳይ ባለሙያ ብቻ እንዳለና በየስራ ክፍሉ እቅድ ላይ እንደማይሳተፍ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፤

54. የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ዕቅድ ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (ሴቶች፣ ወጣቶችና አካል ጉዳተኞችን) ባካተተ መልኩ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት አፈጻጸሙን ያካተተ ሪፖርት በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፤

55. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በኢንስቲትዩቱ የስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል አንድ የሰርዓተ ጾታ ጉዳይ ባለሙያ ብቻ እንዳለና በእቅድ ላይ እየተሳተፈ እንደሆነ ገልፀዋል፤

56. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ፡- በኢንስቲትዩቱ ያለዉ የሥርዓተ ፆታ ባለሙያ አንድ ብቻ ስለሆነ በሥራ ክፍሎች ደረጃ በሚዘጋጁ ዕቅዶች ላይ በቀጥታ ተሳታፊ ባይሆንም በዘርፍ እና በተቋም ደረጃ በሚዘጋጀዉ ላይ ግን በቀጥታ ተሳታፊ እንደሆነ፣ ከዚህ በተጨማሪ በሥራ ክፍሎች ደረጃ ግን እንዴት ስርዓተ ፆታን ማካተት እንደሚችሉ የማማከር አገልግሎት እንደሚሰጥ ገልፀዋል፡፡

57. ይሁን እንጂ በ2008 ዓ.ም በአነስተኛ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ደረጃ ያሉትን በኢንዱስትሪ ሚ/ር መደገፍ ያለባቸው እንደሆነ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በአነስተኛ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የተደራጁትን ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች በመለየት ስራው ላይ በስፋት መገባት እንዳለበት ስለሚታመን የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡

**<u>የኢንስቲትዩቱ ንብረቶች/መሳሪያዎች እና ኬሚካሎች ለብክነት ሳይጋለጡ ስራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን በተመለከተ፡-</u>**

58. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

59. በኢንስቲትዩቱ 165 ዓይነት ንብረቶች ውሳኔ ያላገኙ እና ጥቅም ላይ የማይውሉ፣ 2 ተሽከርካሪዎች እና 8 የእርሻ መሳሪያዎች ውሳኔ ያገኙ ነገር ግን ያልተወገዱ፤ እንዲሁም 81 ዓይነት ንብረቶች/መሣሪያዎች ያረጁና የተበላሹ መሆኑን እና ዘጠኝ አይነት (ዲያዚኖን፣ ዳይሚትዩት፣ ፍላሜብል ሊኪዩድ፣ ሊስትራዚን፣ ስተቪን 85 wp፣ አሲቲክ አሲድ 100%፣ ጽሁፍ የሌለው ፈሳሽ፣ ጽሁፍ የሌለው ዱቄት እና ፒኤች ሜትር) የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈና ጥቅም ላይ የማይውሉ ኬሚካሎች እና የላብራቶሪ መሳሪያዎች መኖራቸውን ተገኝቶ ነበር፤

60. በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሚመለከቱ ሥራን ለማካሄድ በዕቅድ የተገዙ ንብረቶች/መሳሪያዎች እንዲሁም ኬሚካሎች በአግባቡ ሊያዙ፣ ለብክነት

ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸው/የማይሰሩት (Expired/Damaged) የሆኑት የሚወገድበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

61. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሚመለከቱ ሥራን ለማካሄድ በዕቅድ የተገዙ ንብረቶች/መሳሪያዎችለ እንዲሁም ኬሚካሎች በአግባቡ ሊያዙ፣ ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸው/የማይሰሩት (Expired/Damaged) የሚወገዱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ለማድረግ ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

62. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

63. በኢንስቲትዩቱ በቁጥር 63 ዓይነት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈና የተጎዱ (Expired/Damaged) የላብራቶሪ ዕቃዎችና ኬሚካሎች፣ 448 ዓይነት ንብረቶች እና 2 ተሽከርካሪዎች (Nissan patrol ኮድ ET 05045 & Mitsubish ኮድ ET 05044) ውሳኔ ያላገኙ እና ጥቅም ላይ የማይውሉ እንዲሁም 11 የእርሻ መሳሪያዎች እና አንድ ተሽከርካሪ (Defender Land Rover ኮድ ET 02807) ውሳኔ ያገኘ ነገር ግን ያልተወገደ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በተደረገው ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሚመለከቱ ሥራን ለማካሄድ በዕቅድ የተገዙ ንብረቶች/መሳሪያዎች ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸው/የማይሰሩት (Expired/Damaged) በአግባቡ እየተወገዱ እንደሆነ እንዲሁም ሀላፊዎቹ ኬሚካሎችን በተመለከተ ኢንስቲትዩቱ የሚያስወግድበት አግባብ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡ የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በኢንስቲትዩቱ የተለያዩ አይነት ያልተወገዱ ንብረቶች፣ ተሽከርካሪዎች እና ኬሚካሎች በመኖራቸው ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡

65. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ፡-

- ሁለት የማያገለግሉ ተሽከርካሪ የተባሉት ሲንግል ጋቢና 4-05044 እና ኒሣን ፓትሮል 4-05045 የሆኑ ተሽከርካሪዎች በተመለከተ፡ 4-5044 በደረሠበት ከባድ ግጭት ምክንያት የቆመ ሲሆን በአካባቢ አቅም ያለው ጋራዥ ባለመኖሩ አዲስ አበባ ለማስጠገን ቅድመ ሁኔታ በማመቻቸት ላይ እንደሚገኝ፤ 4-05045 በከባድ ብልሽት የቆመና መለዋወጫ በሐገር ውስጥ ያልተገኘለት በመሆኑ አምራች ካምፓኒ ተጠይቆ ከተመረተ ከ10 አመት በላይ ያለፈ ተሽከርካሪ እንደማይቀበል ስለገለፀለ ሌላ አማራጭ ተፈልጎ ከጠፋ የመንግስት ንብረት አወጋገድ ህግን ተከትሎ እንዲወገድ ለመንግስት ግዥ እና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ወደፊት ሪፖርት የሚደረግ መሆኑ ገልፀዋል፡፡
- የእርሻ መሣሪያዎቹ እና ዘጠኝ አይነት ኬሚካል የተባሉት፡ የቀድሞው ኢለሪ ድርጅት በነበሩበት ቦታ ጥሏቸው የሔደ በመሆኑ በተደጋጋሚ ደብዳቤ ተፅፎ የእርሻ መሣሪያዎቹን እንዲያነሱ ቢጠየቅም ኮሚቴና የተለያየ ባለሙያ ልከው ከማሣየትና ፎቶ ግራፍ አንስቶ ከመሔድ በዘለለ ለማንሣት ፍቃደኛ ሣይሆኑ በመቅረታቸው ለመንግስት ግዢና ንብረት ማሰወገድ አገልግሎት እና ለመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሪፖርት የተደረገ ሲሆን ኢንስቲትዩቱ በማንኛውም መንገድ ለማስወገድ የባለቤትነት መብት የሌለው በመሆኑ በቀጣይ በህግ አግባብ ኢለሪ የተባለውን ድርጅት ከሳችሁ ጠይቁ የሚል ምላሽ የተሠጠ ሲሆን ይህን ለማድረግ መ/ቤቱ የህግ ባለሙያ የሌለው በመሆኑ ሊኬድበት እንዳልተቻ ገልፀዋል፡፡

***ኢንስቲትዩቱ በስጋ፣ ወተትና መኖ ሎጀስቲክስ አመራርና ግብይት ዙሪያ ለማቀነባበሪያዎቹ <u>ድጋፍ መስጠትን በተመለከተ፡-</u>***

66. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

67. ኢንስቲትዩቱ በኢንዱስትሪዎቹ ለሚከሰተው የመሣሪያዎች ብልሽትና የመለዋወጫዎች ችግርን አስመልክቶ የሥልጠና እና ድጋፍ አገልግሎት አለመስጠቱ፤ ከኢንስቲትዩቱ ለሥራ ተልከው ወደ ኢንዱስትሪዎቹ የሚሄዱ ባለሙያዎች በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም ላይ እገዛ ለማድረግ የሚያስችል በቂ የተግባር ክህሎት የሌላቸው መሆኑ፤

68. ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ውጤቶች በመዳረሻ ሀገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን በመለየት ለኢንዱስትሪዎቹ ያላስተዋወቀ እና ማስረጃውን ያልሰጣቸው/ያላሰራጨ መሆኑ በናሙና ተመርጠው ከታዩ አራት (ሂሊሜክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ፣ ሉና እና ጅግጅጋ ላይቭስቶክ) ኢንዱስትሪዎች በኦዲቱ ወቅት ከተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ተገኝቶ ነበር፡፡

69. ኢንስቲትዩቱ የዳበረ ልምድ ካላቸው ሀገራት በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም፣ በሥጋ ሎጅስቲክስ አመራርና ግብይት ዙሪያ በእንስሳት ምርቶች ላይ የንግድ ትርኢቶችና ባዛሮችን በማዘጋጀት በገዥ ሀገራት በሚደረጉ መድረኮች ላይ በማስተዋወቅ እና በመዳረሻ ሃገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን እንዲሁም የሥጋ ፍላጎት፣ ዋጋና የተወዳዳሪ ሀገራት የምርት አቅርቦትን በመለየትና እንዲሟላ በማድረግ ለማቀነባበሪያ ፋብሪካዎቹ ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፤

70. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በስጋ ኢንዱስትሪ ልምድ ካላቸው ሀገራት ተግባራዊ ልምድ ያላቸውን ከፍተኛ ባለሙያዎች በልማት አጋሮች ድጋፍ ከአውስትራሊያ፣ ከአሜሪካ፣ ከጀርመን እንዲሁም ከሌሎች ሀገራት በማስመጣት ለኤክስፖርት ቄራዎች ባለሙያ በአጠቃላይ የስጋ አመራረት፣ ጥራትና ደረጃዎች አጠባበቅ፣ በስጋ ብለታና እሽጋ፣ የስጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም እና በተረፈ ምርት አጠቃቀም ላይ ተከታታይ ስልጠና ለመስጠት ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡

71. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

72. በተለያዩ ሀገራት ያሉ የኢትዮጵያ አምባሳደሮች በመጠቀም ለንዑስ ዘርፉ ኢንዱስትሪ ምርቶች ገበያን ለማፈላለግ የሁለትዮሽ ስምምነቶች እንዲፈፅሙ ለማድረግ ከውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ጋር በስፋት ያልተገባበት መሆኑ በ2010 በጀት ዓመት ድጋፍ ስራዎች ዕቅድ ሰነድ በተከለሰበት ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

73. የመዳረሻ ገበያ ውስንነት እና በነባር ገበያዎች ውስጥም ያለ ድርሻ አነስተኛ መሆኑ እንዲሁም የተወሰኑ ገበያዎችና ደንበኞች ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑና ኢንስቲትዩቱ ከውጭ ጉዳይ ሚንስቴር እና ኢንባሲዎች ጋር የጋራ መግባቢያ ስምምነት ስለመፍጠሩና በጋራ ለዘርፉ አማራጭ ገበያ ስለማፈላለጋቸው ማስረጃ አለመገኘቱ በቃለ ጉባኤ 16/01/09 እና የኢንስቲትዩቱ የ2009 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም ሰነድ በተከለሰበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

74. የገዥ ሀገራትን ፍቃድ የማግኘት ሂደቱ የሚዘገይ መሆኑና የሳውዲ የእርድ ተረፈ ምርት ገበያ መዘጋቱ እንዲሁም ኦርጋኒክ ኤክስፖርት ቄራ በሳውዲ ኢንስፔክሽን ቡድን በተሰጠው ግብረ መልስ ከኤክስፖርት መታገዱ፣ አክሽከርና አበርገሌ ህምሌ 2009 ዓ.ም ምንም ኤክስፖርት አለማድረጋቸውን የኢንስቲትዩቱ 2010 በጀት ዓመት ድጋፍ ስራዎች ዕቅድ አፈጻጸም ሰነድ በተከለሰበት ወቅት ለዋወቅ ተችሏል፡፡

75. ኢንስቲትዩቱ በሀገር ውስጥ ባዛር ማዘጋጀት አቅም የሚጠይቅ በመሆኑ እንዳላዘጋጀ፤ ነገር ግን ሌሎች ባዘጋጁት ቄራዎች እንዲሳተፉ እንደሚያደርጉ ለኢንስቲትዩቱ የስራ ሀላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፣

76. በ2009 በጀት ዓመት ሉና፣ ሞጆ ሞደርን፣ ሄልሜክስ (በመዳረሻ ሀገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን ባለማሟላት)፣ ኤልፎራ ደ/ዘይት፣ አበርገሌ (ከዱባይ ገበያ መታገዱ)፣ ሀላል፣ አልነጃም፣ ዴማክ፣ ዮንግታይ እና ጅግጅጋ ኤክስፖርት ቄራዎች በእንስሳት አቅርቦት እጥረት እና የገበያ መዳረሻ ባለመኖሩ ምክንያት እንዲሁም ቄራዎች በሙሉ አቅማቸው ወደ ስራ አለመግባታቸው የኤክስፖርት አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆኑ የኢንስቲትቱ በ2009 በጀት ዓመት የተደረገ ቃለ ጉባኤ በተከለሰበት ወቅት ለዋወቅ ተችሏል፡፡

77. የስጋ ምርት የሚላክባቸው ሀገራት ዱባይና ሳውዳረቢያ ላይ ብቻ የተወሰነ እንደሆነ እና ወደ አውሮፓ እና ሌሎች ሀገራት እንደማይላክ የስጋ ኢንዱስትሪ የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቻው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ ሲሆን፣ የስጋና ወተት ማቀነባበሪያ የሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎችም ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት

ውጤቶች በመዳረሻ ሀገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን በመለየት ለኢንዱስትሪዎች እንዳላሰራጨ ገልፀዋል፡፡

78. በክትትል ኦዲቱ ወቅት የተጠየቁ የስጋ ማቀነባበሪያ የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች ሁሉም ኤክስፖርት ቄራዎች በበረዶ የቀዘቀዘ የዳልጋ ከብት ስጋን መግዛት ወደሚፈልጉ ሀገራት ለምሳሌ፡- አንጎላ፣ ግብጽ፣ ቻይና፣ ኢራን፣ አልጄሪያና ሞሮኮ ኤክስፖርት እንደማያደርጉ ሲገልፁ፣ የስጋ ማቀነባበሪያ፣ ኤክስፖርት ቄራዎችና የወተት ማቀነባበሪያዎች የሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎች ከ2009-2010 በጀት ዓመት በገዥ ሀገራት በሚደረጉ የምርት ማስታወቂያ መድረኮች ላይ ተሳትፈው ምርቶቻቸውን እንዳላስተዋወቁ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

79. ኢንስቲትዩቱ በስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎች ለሚከሰቱ የመሳሪያ ብልሽትና የመለዋወጫ ችግር አስመልክቶ የስልጠናና ድጋፍ አገልግሎት ሰጥቶ እንደማያውቅ፣ ከኢንስቲትዩቱ የሚላኩ ባለሙያዎች በስጋ ብለታና እሽጋ፣ የስጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም ላይ እገዛ ለማድረግ የሚያስችል በቂ የተግባር ክህሎት እንደሌላቸውም በክትትል ኦዲቱ ወቅት የተጠየቁ የስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያ የሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎች ገልፀዋል፡፡

80. በኢንስቲትዩቱ የወተት ዘርፍ የውጪ ምርቶች የገበያ እስትራቴጂ እንዳልተነደፈ፣ ሆላንድ ዴይሪ በይስትና ሞል በወተቱ ላይ በብዛት መገኘት ምክንያት በ2010 ዓ.ም ለአንድ ወር ከሁለት ሳምንት ከገበያ ውጪ እንደተደረጉ፣

81. ጄኔሲስ ፋርም አፍላቶክሲን አለበተግ በሚል ምክንያት በምግብ፣ መድሀኒት፣ ጤና ክብካቤና አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ድርጅታቸው ከመስከረም 2010 ዓ.ም ጀምሮ ኦዲቱ እሰከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ እንደታገደ ነገር ግን ድርጅቱ በራሱ ከኢትዮጵያ ተስማሚነት መዘና ድርጅት እና ከብሌስ አግሮ ላብራቶሪ ኃ.የተ.የግ.ኩባንያ አስመርምሮ ከአፍላቶክሲን ነፃ እንደሆን አረጋግጧል፡፡

82. ለመኖ ማቀነባበሪያ ግብዓትነት የሚያገለግሉ የፋብሪካ ተረፈ ምርቶች ለተደጋጋሚ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንደሚጋለጡና በዚህ ምክንያት የዋጋ ጭማሪ በምርታቸው እንደሚያደርጉ የማቀነባበሪያው የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

83. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከኢንስቲትዩቱ ለሥራ ተልከው ወደ ኢንዱስትሪዎቹ የሚሄዱት ባለሙያዎች በሥጋ ብለታ ላይ ደህና እንደሆኑ ነገር ግን እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም፣ ገፈፋ፣ አለባና የመሳሰሉት ክፍተት እንዳለባቸው እንዲሁም ቴክኖሎጂውን ተከትሎ የሚፈፅም ባለሙያ በኢንስቲትዩቱ እንደሌለና በዘርፉ የሚያሰለጥኑ የሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች እንዳልነበሩ ገልጸዋል፡፡

84. በተጨማሪም የኢንዱስትሪዎች መሣሪያ ብልሽትና የመለዋወጫዎች ችግር ሲከሰት ኢንስቲትዩቱ እንደማይመለከተውና ጣልቃ እንደማይገባ እንዲሁም የኢንስቲትዩቱም ባለሙያዎች የመሳሪያ ጥገና ብቃት እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡

**የስጋ፣ ወተትና መኖ ግብዓት አቅርቦት በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት አስተማማኝ <u>እንዲሆን መደረጉን በተመለከተ፡-</u>**

85. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

86. ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን አቅርቦት እጥረት መንስኤዎችን በመለየት በአቅርቦት ዘርፍ ከተሰማሩ ባለሃብቶችና ተቋማት ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችል ደሰሳ ጥናት (Supply chain) በማካሄድ ተግባራዊ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች እና ለማቀነባበሪያዎቹ ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፣

87. የማሽኒያ፣ የኬሚካል፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎች እና የቁም እንስሳት አቅርቦት በተለይ በሥጋና ወተት ፍላጎትና እንስሳት አቅርቦት ላይ ደሰሳ ጥናት በማከናወን ለማቀነባበሪያዎቹ ያልተሰራጨና ተግባራዊ አለመደረጉ፣

88. የእንስሳት አቅርቦትን ችግር ለመፍታት የግል ባለሃብቶችና የቄራ ባለቤቶች መሬት ወስደው የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል እንዲያረቡ እና እንዲያደልቡ

ብሎም ከይዞታቸው ለእርድ እንዲያቀርቡ የእንስሳት እርባታ (ራንች) እንዲያቋቁሙ አለመደረጉ፤

89. ኤክስፖርት ቄራዎች እንስሳት የሚያቀርቡ ማህበራትና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችና ነጋዴዎችን በመለየት ከቄራዎች ጋር ማስተሳሰር አለመቻሉ በኦዲቱ ወቅት ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎቹ በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ተገኝቶ ነበር፡፡

90. ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ ማደግ ዋናው የግብዓት ምንጭ መሆኑን ተገንዝቦ ለዘርፉ የግብዓት አቅርቦት በዓይነት በመጠን እና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን የግብዓት ኢንዱስትሪዎች እንዲለሙ ሊደግፍ፣ ከጥሬ ዕቃ አመራረት እስከ ዓለም ዓቀፍ ገበያ በምርቶች እሴት ሰንሰለት በዘርፉ ተዋናዮች መካከል ያለው ትስስር ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ምርቶች ፍላጎትና አቅርቦት (Supply Chain) ላይ የደሰሳ ጥናት በማካሄድ ኢንዱስትሪዎቹን ሊደግፍ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

91. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ምርቶች ፍላጎትና አቅርቦት (Supply Chain) ላይ የደሰሳ ጥናት በማካሄድ ኢንዱስትሪዎቹን ለመደገፍ ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

92. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

93. በ2009 በጀት ዓመት ኢንስቲትዩቱ ለስጋ፣ ለወተትና ለመኖ ኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን በተመለከተ እንደ ማሽኒያ፣ ኬሚካል፣ የላብራቶሪና በወተት ፍላጎት ላይ የደሰሳ ጥናት እንዳላከናወነ፣ ይሁን እንጂ በእንስሳት አቅርቦት ዙሪያ እየተከሰተ ያለውን እጥረት ለመፍታት በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በአፋርና የኢትዮጲያ ሶማሌ ክልሎች በተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች ላይ የደሰሳ ጥናት የተሰራ ቢሆንም ጥናቱ ግን ለኢንዱስትሪዎች እንዳልተሰራጨ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፤

94. በ2010 በጀት ዓመት ደግሞ ጥሬ እቃዎችን እንደ ማሽኒያ፣ ኬሚካል፣ ላብራቶሪ፣ የቁም እንስሳት አቅርቦትና በስጋ ፍላጎት ላይ የደሰሳ ጥናት የተከናወነ ቢሆንም ያልታተመና ያልተሰራጨ መሆኑን ለኢንስቲትዩቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል።

95. የእንስሳት አቅርቦትን ችግርን ለመፍታት የግል ባለሀብቶችና የቄራ ባለቤቶች መሬት ወስደው የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል እንዲያረቡና ለእርድ እንዲያቀርቡ የእንስሳት እርባታ/ራንች/ እንዲያቋቁሙ አለማድረጉን የኢንስቲትዩቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

96. ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍ ላይ ለሚገቡ/በስራ ላይ ላሉ ኢንቨስትመንት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን አቅርቦት እጥረት መንስኤዎችን በመለየት በአቅርቦት ዘርፍ ከተሰማሩ ባለሀብቶችና ተቋማት ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችል ደሰሳ ጥናት አለማድረጉን፣ እንዲሁም ከአስራ አንዱ ኤክስፖርት ቄራዎች ውስጥ ለሁለት ቄራዎች (የዳልጋ ከብት ስጋ ኤክስፖርት አድራጊዎች) ብቻ እንስሳት ከሚያቀርቡ አቅራቢዎች ጋር ትስስር እንደፈጠረ የኢንስቲትዩቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል ነገር ግን ለሌሎች ቄራዎች ህጋዊ ትስስር እንዳልፈጠረ ታውቋል፡፡

97. በ2009 ዓ.ም ኦላና እና ኦርጋኒክ የተባሉ ቄራዎች ለእንስሳት መርቢያ ቦታ (ራንች) የወሰዱ ቢሆንም ወደ ተግባር አለመግባታቸውን፣ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ በወተት ማቀነባበሪያዎች አቅራቢያ የሚገኙ ወተት አቅራቢዎች ጋር የማስተሳሰር ስራ እንዳልሰራ፣ ለመኖ ዘርፍ የትምህርት፣ የስልጠና፣ የምርምር ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስር ፎረም ለመተግበር የሚያስችል መመሪያ ወይም ማንዋል የተዘጋጀ ቢሆንም እንዳልጸደቀና ወደ ተግባር እንዳልገቡ የኢንስቲትዩቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

98. ኢንስቲትዩቱ የመኖ ዘርፍን ለማሳደግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት/ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት ጋር የመግባቢያ ሰነድ እንዳልተፈራረሙና በቅንጅትም እንደማይሰሩ የኢንስቲትዩቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

99. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን አቅርቦት እጥረት መንስኤዎችን በመለየት በአቅርቦት ዘርፍ ከተሰማሩ ባለሃብቶችና ተቋማት ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችል የደሰሳ ጥናት (Supply chain) በማካሄድ ረገድ በእንስሳት አቅርቦት ዙርያ የተጠና ጥናት ቢኖርም በወርክ ሾፕ ተደግፎ ወደስራ እንዳልተገባበት እና ገና ወደ ፊት ለመስራትና ተግባራዊ ለማድረግ እንደታሰበ፣
- የማሽጊያ፣ የኬሚካል፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎች እና የቁም እንስሳት አቅርቦት በተለይ በሥጋና ወተት ፍላጎትና እንስሳት አቅርቦት ላይ የደሰሳ ጥናት በማከናወን ለማቀነባበሪያዎቹ ከማሰራጨት ረገድ ከቁም እንስሳት አቅርቦት በስተቀር ጥልቅ የሆነ ጥናት አለመጠናቱና አለመሰራጨቱን፣
- ከሉና ቄራ በስተቀር በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች የመሬት ችግር በመኖሩ ምክንያት የእንስሳት አቅርቦትን ችግር ለመፍታት የግል ባለሃብቶችና የቄራ ባለቤቶች መሬት ወስደው የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል እንዲያረቡ እና እንዲያደልቡ ብሎም ከይዞታቸው ለእርድ እንዲያቀርቡ የእንስሳት እርባታ (ራንች) እንዲያቋቁሙ አለመደረጉ እና ሉናም ሁሉንም ነገር አስጨርሶ የፀደቀለት በ2011 ዓ.ም መሆኑን ገልፀዋል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ለኤክስፖርት ቄራዎች እንስሳት ከሚያቀርቡ አቅራቢዎች ጋር ትስስር መፍጠሩን ቢገልፅም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፣ ኢንስቲትዩቱ በ2009 ዓ.ም በእንስሳት አቅርቦት ዙሪያ እየተከሰተ ያለውን እጥረት ለመፍታት በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ አፋርና የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች በተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች ላይ የደሰሳ ጥናት የተሰራ ቢሆንም ለኢንዱስትሪዎች የሚሰራጨው በደብዳቤ ሳይሆን በወርክሾፕ መሆኑን

ገልፀዋል ነገር ግን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

**ኢንስቲትዩቱ የስጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር <u>በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ፡-</u>**

100. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

101. ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት (በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ግብርና ሚ/ር፣ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ ክልሎች፣ አየር መንገድ፣ ኤርፖርቶች ድርጅት እና ትራንስፖርት ሚ/ር) ጋር በመቀናጀት ውጤታማ የግብይት ሥርዓትን በመዘርጋት አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን በመለየትና በማስተዋወቅ ኢንዱስትሪዎቹ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ማድረግ አለመቻሉ፣ እንዲሁም

102. በዘርፉ የአገር ውስጥ ምርምር አቅም እንዲጠናከር እና የዘርፉን የዝቅተኛና መካከለኛ የሰው ኃይል ፍላጎት እንዲሟላ ሊያደርግ እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራሮችን በመዘርጋት የመግባቢያ ሰነድ (MOU) በመፈራረም ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎችና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ተገኝቶ ነበር፡፡

103. ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ እና በዘርፉ በመሳተፍ ላይ ያሉትን ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን አቅም ለማጎልበት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት (በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ግብርና ሚ/ር፣ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ ክልሎች፣ አየር መንገድ፣ ኤርፖርቶች ድርጅት እና ትራንስፖርት ሚ/ር) ጋር በመቀናጀት መስራት አለበት የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

104.ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ እና በዘርፉ በመሳተፍ ላይ ያሉትን ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን አቅም ለማጎልበት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በቅንጅት ለመስራት ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

105.የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

106.የወተት ማቀነባበሪያዎችን ማህበር በማጠናከር ማቀነባበሪያዎቹ አባል በመሆን እንዲሳተፉ በማድረግ ወደ ተግባር እንዲገቡ ድጋፍ እንዳደረጉ፤ ነገር ግን በቢሮ ችግርና በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በሙሉ አቅማቸው እየሰሩ እንዳልሆነ የኢንስቲትዩቱ ሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፤ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ የወተት ማቀነባበሪያዎችን ማህበር በማጠናከር ሁሉንም ተሳታፊ በማድረግ ማህበራቱ ወደ ተግባር እንዲገቡ ድጋፍ እንዳላደረገላቸው በክትትል ኦዲቱ ወቅት የተጠየቁ የወተት ማቀነባበሪያ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

107.ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ከትምህርት፣ ስልጠና፣ የምርምር ተቋማትና ኢንዱስትሪዎች ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችል የትስስር ፎረምን ለመተግበር የሚያስችል መመሪያና ማንዋል እንዳላዘጋጀና በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ውጤታማ የምርት፣ የቴክኖሎጂና የስልጠና ትስስር እንዲኖራቸው በማድረግ ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ እንዲሸጋገሩ አለማድረጉን የኢንስቲትዩቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

108.የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት (በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት፣

ግብርና ሚ/ር፣ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ ክልሎች፣ አየር መንገድ፣ ኤር ፖርቶች ድርጅት እና ትራንስፖርት ሚ/ር) ጋር በመቀናጀት ውጤታማ የግብይት ሥርዓትን በመዘርጋት አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን በመለየት ለኢንዱስትሪዎች ከማስተዋወቅ አንፃር ከላይ ከተጠቀሱት ባለድርሻ አካላቶች ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ዝቅተኛ መሆኑን፣ ይህም በየጊዜው የሀገሪቱ ችግር ሆኖ የሚጠቀስ ጭምር እንደሆነና መ/ቤቶች በጋራ ለመስራት መነሳሳት የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

- በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ የትምህርት፣ ስልጠና፣ የምርምር ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስር ፎረም ለመተግበር የሚያስችል መመሪያና ማንዋል ዝግጅትን በተመለከተ የስልጠና ማንዋል የተዘጋጀ ቢሆንም ያልፀደቀ መሆኑ እና ለትስስር ፎረም የሚያገለግለው ማንዋል የሳይስና ቴክኖሎጂ ሚንስቴር ያዘጋጀው ማንዋል እንጂ ኢንስቲትዩቱ እንዳላዘጋጀው፣ የትስስር ፎረም በተመለከተ ጅምር ስራዎች ቢኖሩም ከአዳማ አካባቢ ካለው ኮሪደር ማለትም አርሲ ዩኒቨርሲቲ በአካባቢው ከሚገኙ ቄራዎች ጋር ካደረገው ትስስር በስተቀር ወደ ተግባር ያልተገባባቸው መሆኑን እና ትስስሩ በሚፈለገው መጠን አለመሄዱን ገልፀዋል፡፡

**<u>በስጋና ወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ተወዳዳሪ በመሆን ለአገር ውስጥና ለውጭ ሀገር በበቂ ሁኔታ ምርቶችን የሚያቀርቡ ስለመሆኑ፡-</u>**

109.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

110.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በመስክ ሥራ በታዩ ኢንዱስትሪዎች ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ምርቶችን ለመተካት የሚያስችሉ ምርቶችን በሃገር ውስጥ በጥራትና በብዛት እንዲመረቱ የሚያስችል ስልት ኢንስቲትዩቱ ቀይሶ ተግባራዊ አለማድረጉን ለማወቅ መቻሉ፣

111.በወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን በኤክስፖርትና ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባውን ወተት ለመተካት በሚያስችል (Import substitution) ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ እንዲችሉ አለመደረጉ፣

112.የሀገራችን የሥጋ ማቀነባበሪያዎች በተወሰኑ አይነት (በፍየል እና በግ) ሥጋ ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን በሌሎች የተቀነባበረ በዳልጋ ከብት እና ግመል ወ.ዘ.ተ ሥጋ ላይ ግን ትኩረት አድርገው የማይሠሩ መሆኑን፣ እንዲሁም የወተት ማቀነባበሪያዎች ደግሞ ፓስቸራይዝድ ወተት፣ እርጎ፣ አይብ፣ የገበታ ቅቤ እና የምግብ ቅቤ ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን በሌሎች  ክሬም፣ የተፈጨ ቺዝ፣ ፕሮቫለን ቺዝ፣ ሞዞሬላ ቺዝ፣ ፌታ ቺዝ፣ እስሞክድ ቺዝ፣ ፎንቲና ቺዝ ላይ ትኩረት አድርገው የማይሠሩ መሆኑ፤

113.የምርት መጠንን/ብዛትን አስመልክቶ የሥጋ እና ወተት ማቀነባበሪያዎች የማምረት አቅም ያላቸው ቢሆንም በሙሉ አቅማቸው እያመረቱ አለመሆኑ፣ ምክንያቱም ኤክስፖርት ቄራዎች በሙሉ አቅማቸው እንዳይሰሩ ለእርድ የሚቀርቡ እንስሳት በሚፈልጉት ዓይነት፣ ዕድሜ፣ ክብደትና ዋጋ እንዲቀርብ በኢንስቲትዩቱ በኩል ክትትል አለመደረጉ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ኢንዱስትሪዎች እና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

114.ኢንስቲትዩቱ በሥጋና ወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን በኤክስፖርትና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን ወተት ለመተካት በሚያስችል (import substitution) ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ መቅረብ እንዲችሉ በማድረግ ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ምርቶችን ለመተካት የሚያስችሉ ምርቶች በአገር ውስጥ በጥራትና በብዛት እንዲመረቱ ሊያደርግ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

115.ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ምርቶችን ለመተካት የሚያስችሉ ምርቶችን በሃገር ውስጥ በጥራትና በብዛት እንዲመረቱ የሚያስችል ስልት ለመቀየስና ተግባራዊ ለማድረግ ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

116.የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

117.የኤክስፖርት ቄራዎች እና የወተት ማቀነባበሪያዎች በሙሉ አቅማቸው አለመስራታቸው እና በውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ምክንያት ዝቅተኛ አፈፃፀም

ማሳየታቸው ታውቋል፡፡ ለአብነትም፡- በ2009 በጀት ዓመት ሃሽም ኤክስፖርት ቄራ 30.95 በመቶ፣ ኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ 43.62 በመቶ፣ አቢሲንያ ኤክስፖርት ቄራ 60.30 በመቶ፣ ሀላል ኤክስፖርት ቄራ 48.33 በመቶ፣ አልነጃም ኤክስፖርት ቄራ 22.79 በመቶ፣ ዮንግታይ የእርድ ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ 29.73 በመቶ እና አክሸከር እርድ ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ደግሞ 5.01 በመቶ ብቻ ኤክስፖርት ማድረጋቸው በኢንስቲትዩቱ የ2010 በጀት ዓመት የድጋፍ ስራዎች እቅድ ላይ የተገለጸ መሆኑ፤

118. የተረፈ ምርት ላኪዎች (አክሽከር፣ ዮንግታይ፣ ዳማክ፣ በላይነህ እና የመሳሰሉት) ምርታቸውን አከማችተው የሚልኩ በመሆኑ ለ2009 በጀት ዓመት ኤክስፖርት አፈፃፀም ማነስ ምክንያት እንደሆነ ከተከለሱ የኢንስቲትዩቱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡

119. የመዳረሻ ገበያ ውስንነት፣ የእርድ እንስሳት አቅርቦት ችግር፣ የመብራትና ሌሎች መሰረተ ልማቶች አቅርቦት ችግሮች፣ በዕቅድ ታሳቢ የሚደረጉ ድርጅቶች ወደ ስራ ያለመሰማራት ችግር፣ የሎጅስቲክስ ችግሮች፣ የህግ የግብይት ማዕቀፍ አለመኖር፣ የምርት ስብጥር አለመኖር እና በድርጅቶች የውስጥ አሰራር ችግሮች በተደጋጋሚ ለኤክስፖርቱ አፈፃፀም ማነስ ምክንያቶች እንደሆኑ መጠቀሳቸው በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

120. በ2010 በጀት አመት ደግሞ ኦላና ኤክስፖርት ቄራ 13,227 ቶን (47.30 ሚሊዮን ዶላር) የስጋና ተረፈ ምርት ኤክስፖርት ለማድረግ ታቅዶ የእቅዱን 373.51 ቶን (2.24 ሚሊዮን ዶላር) ይኸውም የዕቅዱን 5.12% ብቻ ያሳካ መሆኑ፣ አበርገሌ ኤክስፖርት ቄራ በ2010 በጀት አመት ምንም አይነት ምርት አለመላኩ፣

121. ኢኒስቲትዩቱ በ2010 በጀት አመት ከዘርፉ 40,172 ቶን (180.35 ሚሊዮን ዶላር) የስጋና ዕርድ ተረፈ ምርት ኤክስፖርት ለማድረግ አቅዶ የእቅዱን 20,547.75 ቶን (103.3 ሚሊዮን ዶላር) ማለትም 51% ብቻ ያሳካ መሆኑ፤ እንዲሁም 4,300 ሊትር (0.64 ሚሊዮን ዶላር) ኤክስፖርት ለማድረግ አቅዶ የእቅዱን 1,537.24 ሊትር (103.3 ሚሊዮን ዶላር) ማለትም 35.75% ብቻ ያሳካ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

122.በ2010 በጀት አመት በአንድ ሳምንት ከ8 ኤክስፖርት ቄራዎች ማለትም አክሽከር 189.10 ቶን (0.9663 ሚሊዮን ዶላር)፣ ሉና 78.09 ቶን (0.399 ሚሊዮን ዶላር)፣ ሞጆ 80.50 ቶን (0.411 ሚሊዮን ዶላር)፣ ሀላል 76350 ቶን (0.390 ሚሊዮን ዶላር)፣ ኦርጋኒክ 30.50 (0.156 ሚሊዮን ዶላር)፣ ሀሽም 10 ቶን (0.051 ሚሊዮን ዶላር)፣ አቢሲኒያ 6.50 ቶን (0.033 ሚሊዮን ዶላር) እና ኤልፎራ 6.00 ቶን (0.031 ሚሊዮን ዶላር) በድምሩ 477.89 ቶን ስጋ (2.438 ሚሊዮን ዶላር) ትእዛዝ መሰረዙ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

123.በ2009 በጀት ዓመት ኑረዲን ወተት ማቀነባበሪያ ድርጅት (አ/አ) በሳምንት 95,666 ሊትር ወተት ለማቀነባበር አቅዶ 22,960 ሊትር ማለትም 24 በመቶ ያከናወነ መሆኑ፣ አልሚ ትኩስ ወተት ማቀነባበሪያ ድርጅት (ሀዋሳ) በሳምንት 76,712 ሊትር ወተት ለማቀነባበር አቅዶ 8,400 ሊትር ማለትም 10.95 በመቶ ያከናወነ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

124.ኢንስቲትዩቱ ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ምርቶችን ለመተካት የሚያስችሉ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በጥራትና በብዛት እንዲመረት የሚያስችል ስልት እንዳልቀየሰና ማቀነባበሪያዎቹም በሙሉ አቅማቸው እንደማይሰሩ፣ ለስጋ ማቀነባበሪያዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ ለእርድ የሚቀርቡ እንስሳት ኤክስፖርት ቄራዎች በሚፈልጉት ዓይነት፣ ዕድሜ፣ ክብደትና ዋጋ እንዲቀርብላቸው ክትትል እንደማያደርግ ለኢንስቲትዩቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

125.የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- ኢንዱስትሪዎች ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ምርቶችን ለመተካት የሚያስችሉ ምርቶችን በሃገር ውስጥ በጥራትና በብዛት እንዲመረቱ የሚያስችል ስልት ኢንስቲትዩቱ ቀይሶ ተግባራዊ ያላደረገበት ምክንያት እና ሁሉንም ፋብሪካዎች ሙሉ በሙሉ ድጋፍ በማድረግ ተወዳዳሪ ማድረግ ያልተቻለው ኢንስቲትዩቱ ካለው የአቅም ማነስ እንደሆንና በተወሰነ ደረጃ አየር መንገድ የሀገር ውስጥ የወተት ውጤቶች እንዲጠቀም የተደረገበት ሁኔታ መኖሩና

ወደፊት ኢንቨስትመንት በማስፋፋት ገቢ ምርቶችን ማስቀረት እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

- በተጨማሪም ሀገሪቷ ያላት የእንስሳት ዝርያ የአለም አቀፍ መስፈርትን ስለማያሟላና የአቅርቦት እጥረት ስላለ፣ እንዲሁም በህገ ወጥ መልኩ እንስሳት ከሀገር ስለሚወጡና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ያልተሄደበት በመሆኑ እንዲሁም እንስሳት በእድሜ፣ በአይነትና በክብደት ማግኘት የሀገራችን ችግር መሆኑን ገልፀዋል፡፡

<u>ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ የወተትና የመኖ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ማድረጉን በተመለከተ፡-</u>

126.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

127.በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎች ያልተዘጋጁና ያልተሰራጩ መሆኑ፤ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሃብቶች ጠቋሚ ጥናት በማድረግ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል በማድረግ እንዲሁም በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ያነጋገራቸው የሉሜ፣ ጅግጅጋ እና ሃዋሳ ከተማ መስተዳደር ኢንዱስትሪ የስራ ሂደት የበላይ ኃላፊዎች የገለጹ ሲሆን፤ በአፈጻጸም ወቅትም ለተከሰቱ ችግሮች ስለተሰጠው የማስተካከያ እርምጃ የሚያመለክት ማስረጃ በናሙና ከታዩት ማቀነባበሪያዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ማግኘት አለመቻሉ ተገኝቶ ነበር፡፡

128.ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችል የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ሊያዘጋጅና ሊያሰራጭ፣ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሃብቶች ጠቋሚ ጥናት ሊያደርግ፣ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ሊሰጥ፣ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሊያካሂድ እና በዘርፉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲወገዱ ድጋፍ በመስጠት አዳዲስ ባለሃብቶች በዘርፉ በብዛት እንዲሰማሩ ሊያደርግ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

129.ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንደስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎች ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

130.የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

131.ወደ ማምረት ተግባር ይገባሉ ተብለው ታሳቢ የተደረጉ ኤክስፖርት ቄራዎችና ፕሮጀክቶች በወቅቱ ስራ አለመጀመራቸው፣ በኢንስቲትዩቱ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች ጠቃሚ ጥናት በማጥናት በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል በማድረግ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል ስርዓት እንዳልተዘረጋ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በታዩ ፋብሪካዎች በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

132.ኢንስቲትዩቱ አነስተኛና መካከለኛ አምራቾች ኢንቨስትመንታቸውን ለማሳደግ የማስተዋወቅ ስራ እንደሰራ፤ ነገር ግን አጥጋቢ/በቂ እንዳልሆነ፣ አደአ የወተት ህብረት ሥራ ማህበር የተመጣጠነ የእንስሳት መኖን በቀን በሶስት ጊዜ ፈረቃ ከ750 ኪ.ግ በላይ ማቀነባበር የሚያስችለው መሳሪያ ያለው ቢሆንም የክትትል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አገልግሎት መስጠት እንዳልጀመረ ታውቋል፡፡

133.ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት የሚያስችል የፕሮጀክት ፕሮፋይልና የአዋጭነት ጥናት ያዘጋጀ ቢሆንም የፕሮጀክት ፕሮፋይሉና የአዋጭነት ጥናቱ ህጋዊ ሆኖ ስለመታተሙና በወርክሾፕ ታግዞ ለሚመለከታቸው አካላት የማስተዋወቅ ስራ ስለመሰራቱ የሚያሳይ መረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

134. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- በኢንስቲትዩቱ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች ጠቃሚ ጥናት በማጥናት በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል በማድረግ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ

ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርዓቱ የስምሪት እቅድ እንደሆነ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያላቸው ቅንጅታዊ አሰራር ዝቅተኛ ስለሆነ ድርጅቶችን ከጅምሩ ለይቶ ጠቋሚ ጥናት ለማጥናት እንደማይቻል ገልፀዋል፡፡

- እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት የሚያስችል የፕሮጀክት ፕሮፋይልና የአዋጭነት ጥናት የማዘጋጀቱ ጉዳይ እንደ ኢንስቲትዩቱ አቅም የተሄደበት መሆኑን ነገር ግን በቂ እንዳልሆነና ወደፊት የኢንስቲትዩቱ አቅም ሲጠናከር ትኩረት በመስጠት እንደሚያሻሽሉ ገልጸዋል፡፡

***በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ዙሪያ ያሉ መልካም ተሞክሮዎች ተቀናብረው ተግባራዊ የተደረጉ ስለመሆኑ፡-***

135.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

136.ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸውን ሃገራትና ካምፓኒዎችን ለይቶ ተሞክሮዎቹን አቀናብሮ ለማቀነባበሪያዎቹ የማያሰራጭና ተግባራዊነቱን የማይከታተል መሆኑ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች ለማወቅ መቻሉ፤

137.በኢንስቲትዩቱ የተቀናበሩና የተሰራጩ መልካም ተሞክሮ ሰነዶች ኢንዱስትሪዎቹ ተጠይቀው ማቅረብ አለመቻላቸው እና የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎችም ወደ ውጪ ሃገር ሄደው ከመጡ በኋላ ለማቀነባበሪያዎቹ ስላዩዋቸው ተሞክሮዎች ያገኙትን ልምድ የማያካፍሏቸው መሆኑ በናሙና ተመርጠው የታዩት ሶስት የሥጋ (ሂልሜክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ እና ሉና) ፣ ስድስት የወተት (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ጂኔሲስ ፋርም፣ ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) እና ሁለት የመኖ (አዲስ አለም ሞጆ እና አለማ ካዋዳይስ) ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎቹ በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ተገኝቶ ነበር፡፡

138.ኢንስቲትዩቱ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ እና የኢንዱስትሪዎቹን ዕውቀትና ክህሎት ለማሳደግ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ

ያላቸው ሃገራትና ካምፓኒዎች ተለይተው ተሞክሮዎቹ ተቀናብረው በኤክስፖርት ቁራዎች፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ተግባራዊ (implement) ሊያደርጉ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

139. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ኢንስቲትዩቱ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ እና የኢንዱስትሪዎቹን ዕውቀትና ክህሎት ለማሳደግ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሃገራትና ካምፓኒዎች ተለይተው ተሞክሮውን ለማቀነባበሪያዎቹ ለማሰራጨት/ለማድረስ ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

140. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

141. ኢንስቲትዩቱ በስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሀገራትና ካምፓኒዎችን ለይቶ ተሞክሮዎቹን ቀምሮ/አቀናብሮ ለማቀነባበሪያዎቹ እንዳላሰራጨ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡

142. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሃገራትና ካምፓኒዎችን ለይቶ ተሞክሮዎቹን አቀናብሮ ለማቀነባበሪያዎቹ የማሰራጨቱ ጉዳይ የኢንስቲትዩቱ የመፈፀም አቅም ዝቅተኛ ስለሆነ መልካም ተሞክሮዎች ተቀናብረው እንዳልተሰራጩ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ኢንዱስትሪዎቹ ውጪ ሀገር ሂደው ልምድ እንዲያገኙ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ ባለው ዝቅተኛ የመፈፀም አቅም በሚል ምክንያት ለዘርፉ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሃገራትና ካምፓኒዎችን ለይቶ ተሞክሮዎቹን አቀናብሮ አለማሰራጨቱ አግባብነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም እንዲሁም በክትትል ኦዲቱ ወቅት መልካም ተሞክሮ ተቀናብሮ ለዘርፉ ኢንዱስትሪዎች ስለመሰራጨቱ የሚገልፅ ማስረጃ ባለመቅረቡ ምላሹን ለመቀበል አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተደራጁና ለሚመለከተው አካል የተሰራጩ መሆኑን በተመለከተ፡-**

143.በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

144.ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያና ሌሎች መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን እና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ሊያሰራጭ አለመቻሉ፣

145.የእንስሳት ዱካን (Tracibility) ለመመዝገብ የሚያስችል መዝገብ (records) እንዲዘጋጅና ተግባራዊ እንዲደረግ በማድረግ የእንስሳት ጤና ሥርዓትና ቁጥጥርን አስመልክቶ መረጃዎችን ለተቀባይ ሀገራት የማድረስና የማስተዋወቅ ሥራ አለማከናወኑ በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች እና ከኢንስቲትዩቱ ተሰብስበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ተገኝቶ ነበር፡፡

146.ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ፣ ለኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎችን ዝርዝር፣ የክልሎችን የእንስሳት አቅርቦት መጠን፣ የወተት ሃብትና የመኖ ማምረት አቅም እንዲሁም ሌሎች መረጃዎች በማሰበሰብ፣ በመተንተንና በመረጃ ቋት/በዳታቤዝ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች በቀላሉ መስጠት ይጠበቅበታል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

147.ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ፣ ለኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎችን ዝርዝር፣ የክልሎችን የእንስሳት አቅርቦት መጠን፣ የወተት ሃብትና የመኖ ማምረት አቅምና ሌሎች መረጃዎች በማሰበሰብ፣ በመተንተን እና በመረጃ ቋት/በዳታቤዝ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ለማድረስ ከ2009በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

148.እንዲሁም የእንስሳት ዱካን (Tracibility) ለመመዝገብ የሚስችል መዝገብ ማዘጋጀት በዋናነት የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ሚኒስቴር ስራ እንደሆነና ካለው ፋይዳ አንጻር ከኢንስቲትዩቱ ሰው ተመድቦ በጋራና በቅንጅት ለመስራት የተጀመረ ስራ እንዳለና ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ የቅድመ ዝግጅት ስራ እንደሚሰራና በ2009 በጀት ዓመት የካቲት ወር ጀምሮ በቦረና ዞን እና በትግራይ ክልል አበርገሌ ተፋሰስ የተግባር ስራ እንዲጀመር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

149.የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

150.ኢንስቲትዩቱ ለስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ፣ ለኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎች ዝርዝር፣ የክልሎችን የእንስሳት አቅርቦት መጠን፣ የወተት ሀብትና የመኖ የማምረት አቅምና ሌሎች መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተን እና በመረጃ ቋት/በዳታቤዝ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች እንደማያሰራጭ በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች እና ከኢንስቲትዩቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እንዲሁም ከኢንስቲትዩቱ ተሰብስበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

151.ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ዱካን (Tracibility) ለመመዝገብ የሚያስል መዝገብ (records) እንዲዘጋጅና ተግባራዊ እንዲደረግ በማድረግ የእንስሳት ጤና ሥርዓትና ቁጥጥርን አስመልክቶ መረጃዎችን ለተቀባይ ሀገራት የማድረስና የማስተዋወቅ ሥራ አለማከናወኑ በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች እና ከኢንስቲትዩቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ እንዲሁም ከኢንስቲትዩቱ ተሰብስበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡
፡

152.የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- ኢንስቲትዩቱ ለስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ፣ ለኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎች ዝርዝር፣

የክልሎችን የእንስሳት አቅርቦት መጠን፣ የወተት ሀብትና የመኖ የማምረት አቅም እንዲሁም ሌሎች መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተን እና በመረጃ ቋት/በዳታቤዝ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች የማያሰራጭ መሆኑን፣ ምክንያቱም ኢንስቲትዩቱ የተዘጋጀ ዳታ ቤዝ ሲስተም የሌለው መሆኑና ከክልሎች ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ደካማ በመሆኑ እና ይህንን ተግባር ለማከናወን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በክልል እንደሌለው ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ ክልሎች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ሊያጠናከር እና ዳታ ቤዝ ሲስተም በመዘርጋት ለዘርፉ ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ፣ ለኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎች ዝርዝር፣ የክልሎችን የእንስሳት አቅርቦት መጠን፣ የወተት ሀብትና የመኖ የማምረት አቅም እንዲሁም ሌሎች መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተን እና በመረጃ ቋት/በዳታቤዝ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ማድረስ ተገቢ ስለሆነ ምላሹን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

- እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ዱካን (Tracibility) ለመመዝገብ የሚያስችል መዝገብ (records) እንዲዘጋጅና ተግባራዊ እንዲደረግ በማድረግ የእንስሳት ጤና ሥርዓትና ቁጥጥርን አስመልክቶ መረጃዎችን ለተቀባይ ሀገራት የማድረስና የማስተዋወቅ ሥራ ያላከናወነበት ምክንያት ይህ ተግባር በግብርና ሚንስቴር የሚከናወን በመሆኑ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

153. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሀላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ፡-

- በሀገራችን ከእንስሳት በሽታ ነፃ የሆነ ቀጠና እንዲሁም የእንስሳት ልየታና የምዝገባ ስርዓት ባለመኖሩ ምክንያት የተሻለ ዋጋ ሊከፍሉ በሚችሉ የዓለም የሥጋ ገበያ ዉስጥ መግባት እንዳልተቻለ እንዲሁም ከተግባርና ኃላፊነት አንፃር የእንስሳት ልማቱ ኢንስቲትዩቱ ባይመለከተውም ኢንስቲትዩቱ የሚደግፋቸዉን ፋብሪካዎች እስከ ጎዳ ድረስ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ለመስራት ጥረት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የቴክኒካል ኮሚቴው አባል በመሆን የጋራ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ እንደገቡ እንዲሁም ለወደፊት ዘርፉን ማጠናከር እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል፡፡

**ኢንስቲትዩቱ ሥጋና ወተት መዳረሻ ገበያ እስኪደርስ ድረስ ክትትል እና ቁጥጥር <u>በማድረግ ለቄራዎች ግብረ መልስ በመስጠት አፈጻጸሙን ያሳደገ መሆኑን በተመለከተ፡-</u>**

154. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

155. ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ስጋን ጥራቱን ጠብቆ እንዲሄድ የሚያደርገው የኮልድ ቼይን ሥርዓት ኤርፖርት አካባቢ ላይ የሚቋረጥበት ሁኔታ መኖሩ፣ ኤርፖርት/ካርጎ/ ሥጋ በማውረድ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች ስለ ሥጋ አያያዝና አጠባበቅ በቂ ዕውቀት ስለሌላቸው መኪኖችን ክፍት ትተው በመሄድ ሥጋውን ለሙቀት እንዲጋለጥ የሚያደርጉበት እና ሥጋውን በሚሸከሙበት ወቅት በአግባቡ የማይዙ እንዲሁም ሥልጠና የተሰጣቸው ቢሆንም በተግባር ክትትል ስለማይደረግባቸው ችግሩ አሁንም እየተስተዋለ መሆኑ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ ከታዩ ሶስት (ሃሽም/ሄልሜክስ፣ ኤልፎራ እና ሉና ቄራዎች) በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ተገኝቶ ነበር፡፡

156. ኢንስቲትዩቱ ሥጋና ወተት ወደ ሚላኩባቸው መዳረሻ ገበያዎች እስኪደርሱ ድረስ የክትትል ሥራ በማድረግ ለቄራዎች እና ለወተት ማቀነባበሪያዎች ግብረ-መልስ በመስጠት የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበሩ በማድረግ የማቀነባበሪያዎቹን አፈጻጸም ሊያሳድግ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

157. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ኢንስቲትዩቱ ሥጋና ወተት ወደ ሚላኩባቸው መዳረሻ ገበያዎች እስኪደርሱ ድረስ የክትትል ስራ /ሱፐርቪዥን ሥራ/ በማድረግ ለቄራዎች እና ለወተት ማቀነባበሪያዎች ግብረ-መልስ በመስጠት የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበሩ ለማድረግ ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

158. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

159. ኢንስቲትዩቱ ስጋና ወተት ወደሚላክባቸው መዳረሻ ገበያዎች እስኪደርስ ድረስ ሱፐርቪዥን በማድረግ ለቄራዎችና ለወተት ማቀነባበሪያዎች ግብረ መልስ እንዳልሰጣቸው እና በቄራዎቹም ጥራቱን ጠብቆ የሚሄደው ኮልድ ቼይን ስርዓት ኤርፖርት /ካርጎ/ አካባቢ የሚቋረጥበት ሁኔታ መኖሩንና ዓለም አቀፍ መስፈርትን

ያሟሉ ምርቶችን ለሀገር ውስጥና ለዓለም ገበያ በስፋት እንደማያቀርቡ በክትትል ኦዲቱ ወቅት የታዩ የስጋና ወተት ማቀነባበሪያዎች የሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎች በተደረገላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

160. በኦዲቱ ወቅት የታዩ ቄራዎች ምርታቸው በሁለት የአረብ ሀገራት ላይ ብቻ የተወሰነ እንደሆነና ስጋትም እንደፈጠረባቸው፣ እንዲሁም የወተት ማቀነባበሪያዎች የወተት ኤክስፖርት ዕቅድ እንደማያዘጋጁና ወተትና የወተት ውጤቶች ወደ ውጭ እንዲልኩ ማድረግ አለመቻሉን ከማቀነባበሪያዎቹ የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

161. ኤርፖርት አካባቢ ስጋ በማውረድ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች ስለ ስጋ አያያዝና አጠባበቅ ላይ በቂ እውቀት እንደሌላቸውና ኢንስቲትዩቱም ለሰራተኞቹ በተግባር ላይ የተደገፈ ስልጠና እንዳልሰጠና ክትትል እንዳላደረገ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

162. እንዲሁም ኤርፖርት አካባቢ ስጋ በማውረድ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች ስለ ስጋ አያያዝና አጠባበቅ በቂ እውቀት የሌላቸው በመሆኑ ምክንያት በምርቱ ላይ ብልሽት እንደሚደርስበትና ኢንስቲትዩቱ ችግሩን ለመፍታት ጥረት እንዳላደረገ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተጠየቁ የስጋ ማቀነባበሪያ ሀላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ታውቋል፡፡

163. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- ኢንስቲትዩቱ ስጋና ወተት ወደሚላክባቸው መዳረሻ ገበያዎች እስኪደርስ ድረስ ሱፐርቪዥን በማድረግ ለቄራዎችና ለወተት ማቀነባበሪያዎች ግብረመልስ እንደማይሰጥ፣ በቄራዎቹም ጥራቱን ጠብቆ የሚሄደው ኮልድ ቼይን ስርዓት ኤርፖርት /ካርጎ/ አካባቢ የሚቋረጥ መሆኑና ይህም ተግባር በኢንስቲትዩቱ ሳይሆን በግብርና ሚንስቴር የሚከናወን እንደሆነ ገልፀዋል፤
- የስጋና ወተት ማቀነባበሪያዎች ዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟሉ ምርቶችን ለዓለም ገበያ በስፋት የማያቀርቡበት ምክንያት የዘርፉ አለም አቀፍ መስፈርት ከእኛ ሀገር ነባራዊ ሁኔታ ጋር ስለማይጣጣምና ከኢትዮጵያ ደረጃ በጣም ከፍ ያለ በመሆኑ እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን

በቅንጅት የመስራቱ ሁኔታ ደካማ በመሆኑ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ለማሻሻል አስቸጋሪ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

164. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሀላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ በአየር መንገድ ያሉት ሰራተኞችን በሚመለከት በ2008 በጀት ዓመት ከግብርና ሚንስቴር ጋር በመሆን ለስጋ አውራጅ እና ጫኝ የአየር መንገድ ሰራተኞች ስልጠና እንደሰጡ ገልፀዋል፡፡

165. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ፡-

- ኢንስቲትዩቱ ሥጋና ወተት ወደ ሚላኩባቸው መዳረሻ ገበያዎች እስኪደርሱ ድረስ ሱፐርቪዥን ሥራ በማድረግ ለቄራዎች እና ለወተት ማቀነባበሪያዎች ግብረ- መልስ በመስጠት የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገብሩ በማድረግ የማቀነባበሪያዎቹን አፈጻጸም ሊያሳድግ እንደሚገባው ስለሚታመን የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፤
- ኢንስተቲትየቱ የስጋና ወተት ማቀነባበሪያዎች ዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟሉ ምርቶችን ለዓለም ገበያ በስፋት ማቅረብ እንዲችሉና ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት ያለባትን ጥቅም ለማግኘት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ቅንጅታዊ አሰራሩን በማጎልበት መስራት እንዳለበት ተገቢ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፤
- እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ በአየር መንገድ ያሉት ሰራተኞችን በሚመለከት በ2008 በጀት ዓመት ከግብርና ሚንስቴር ጋር በመሆን ለስጋ አውራጅ እና ጫኝ የአየር መንገድ ሰራተኞች ስልጠና እንደሰጡ ቢገልፁም በ2009ና 2010 በጀት ዓመት ለስጋ አውራጅ እና ጫኝ የአየር መንገድ ሰራተኞች ስልጠና ባለመሰጠቱና ለነዚሁ ሰራተኞች ወጥ የሆነ የስልጠና ፕሮግራም ባለመኖሩ ከላይ የተሰጠው ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

**ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር ላይ ተሳትፈው ውጤት ያላስመዘገቡ ኢንዱስትሪዎችን በመለየት የኢንቨስትመንት ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረጉን በተመለከተ፡-**

166. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

167. ኢንስቲትዩቱ ከክልሎችና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየት ኢንቨስትመንት ውሳኔ እንዲያገኙ ሊያደረግ አለመቻሉ ተገኝቶ ነበር፡፡

168. ኢንስቲትዩቱ ከክልሎችና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታ ያልጀመሩ፣ ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየትና የገጠማቸውን የኢንቨስትመንት ማነቆ በመፍታት ወደ ሥራ እንዲገቡ ሊያደርግ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

169. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር ኢንስቲትዩቱ ከክልሎችና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየት የኢንቨስትመንት ውሳኔ እንዲያገኙ ለማድረግ ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

170. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

171. በኢንስቲትዩቱ የካቲት 2009 ዓ.ም በተደረገ የደሰሳ ጥናት በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር ላይ መሬት ወስደው ወደ ስራ ካልገቡ ኢንዱስትሪዎች መካከል በኦሮሚያ ክልል 19፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር 10፣ በአማራ ክልል 42፣ በሀረሪ ክልል 17 እና በደቡብ ክልል 44 ባለሀብቶች መኖራቸው ታውቋል፤ ነገር ግን እነዚህ በጥናት የተለዩት ባለሃብቶች የኢንቨስተመንት ውሳኔ እንዲያገኙ ለሚመለከተው አካል እንዲያውቀው የተደረገበት ማስረጃ ክትትል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፤

172. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት ምላሽ፡-

- ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ውጤቶችና የእንስሳት መኖ ለማቀነባበር የሚፈልጉ አካላት/ባለሀብቶች በጥናት እንዲቋቋሙ የማድረጉ ጉዳይ ትልቅ ትኩረት የሚሻ መሆኑ እንደሚያምንበትና ይህም ለማሳካት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራትን ቀዳሚ ተግባር እንደሆነ ያምንበታል ሆኖም ግን ያለው ቅንጅታዊ አሰራር በጣም ደካማ መሆኑ እና የሚቋቋሙት ባለሃብቶች ከኢንስቲትዩቱ ከመምጣታቸው በፊት ፋብሪካዎች በራሳቸው ኢንስቲትዩቱ ሳያውቅ የሚቋቋሙበት አግባብ መኖሩና ካለው ደካማ ቅንጅታዊ አሰራር የተነሳ ኢንስቲትዩቱ ይህን ለማድረግ ያልቻለ መሆኑ ገልፀዋል፤
- በኢንቨስትመንት ውሳኔ ዙሪያ እርምጃ የመውሰድ ሥራ በዋናነት የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኃላፊነት እንደሆነና ኢንስቲትዩቱ ለባለሀብቶች ወደ ንዑስ ዘርፉ እንዲገቡ ከሚሰጠው ድጋፍ ባልተናነሰ በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታቸውን የሚያዘገዩትንም ሆነ ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለሚመለከተው አካል ሲያሳውቅ የቆየ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

173. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ኢንስቲትዩቱ ማቀነባበሪያዎቹ ሲቋቋሙ ጀምሮ በጥናት እንዲቋቋሙ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ትስስር በመፍጠር በጥናት እንዲቋቋሙ በማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ የሚጠበቅበት በመሆኑ እና የኢንቨስተመንት ውሳኔ እንዲያገኙ ለሚመለከተው አካል እንዲያውቀው የተደረገበት ማስረጃ ባለመቅረቡ ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡

**<u>በኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ውጤታማነትን በተመለከተ፡-</u>**

174. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

175. በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በስልጠና ፍላጎት ደሰሳ ጥናት (need assessment) ላይ የተሞረከዙ እና ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሁም ተግባር ተኮር ሥልጠዎች አለመሆናቸውን ከሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች የበላይ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፣

176. ሥልጠናው የሥጋ እና የወተት ገበያ በቀዘቀዘ ወቅት (ለወተት ማቀነባበሪያዎች በጾም ወቅት እና ለሥጋ ማቀነባበሪያዎች ሥጋ ወደ አረብ ሀገራት የሚልክ በመሆኑ ከአረፋ እና ከሌሎች የሙስሊም በዓላት ወቅት ውጪ) ላይ ብቻ የማይሰጥ በመሆኑ ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከታቸውን ባለሙያ ለመላክ የሚገደዱ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማቀነባበሪያዎቹ በቀረቡ ቼክ ሊስቶች እና ቃለ መጠይቅ ተገኝቶ ነበር፡፡

177. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ከሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች በዕቅድ ላይ የተመሰረቱ፣ ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሁም ውጤታቸውም መለካት የሚቻል መሆን አለበት የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

178. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ ከሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች በዕቅድ ላይ የተመሰረቱ፣ ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሁም ውጤቱንም ለመለካት ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

179. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

180. በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በደሰሳ ጥናት (need assessment) ላይ የተመረኮዙ እና ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሁም ተግባር ተኮር ሥልጠና አለመሆኑን ከሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች የበላይ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፤

181. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በደሰሳ ጥናት (need assessment) ላይ መሰረት ያደረጉና ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሁም ተግባር ተኮር ሥልጠና መሆናቸው ገልፀዋል፤
- እንዲሁም የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሀላፊዎች ለክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡት ስልጠናዎች በእቅድ የተያዙና ተግባር ተኮር ስልጠና እንደሆነ የ2010 በጀት ዓመት የኢንስቲትዩቱ ዕቅድ አፈፃፀም ገፅ 14 ላይ ያለውን እንደማሳያ በመጠቀም የገለፁ ቢሆንም ኦዲቱ

እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ በዕቅድ የተያዘና ተግባር ተኮር ስልጠና ስለመሰጠቱ የሚገልፅ ማስረጃ ባለመቅረቡና በተመሳሳይ መልኩ ለወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎች በእቅድ የተያዘና በተግባር ላይ የተመሰረተ ስልጠና ስለመሰጠቱ የሚገልፅ ማስረጃና የስልጠና ጥሪ ደብዳቤ ባለመቅረቡ እንዲሁም ስልጠናው ተሰጥቶ ከሆነ ከስልጠናው በኋላ ስልጠናው ስላስገኘው ጠቀሜታ ደሰሳ ጥናት በማድረግ የማረጋገጥ ስራ ስላልተሰራ ከላይ የተገለፀውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

**በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎችን በመስክ በመከታተል የአፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ፡-**

182. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

183. ኢንስቲትዩቱ በነባር፣ ሥራ በጀመሩ እና በግንባታ ላይ ያሉ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሥራ እንቅስቃሴ በመስክ በመከታተልና በየካምፓኒው ደረጃ እንዲጠናቀሩ በማማከር ኢንስቲትዩቱ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የስድስት ወር፣ ዘጠኝ ወር እና ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት የሚያቀርብ ቢሆንም የኢንዱስትሪዎቹን የሥራ እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችለውን ሪፖርት ከማቀነባበሪያዎቹ በተከታታይ ማግኘት የሚያስችለውን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፤

184. ኢንስቲትዩቱ በየዓመቱ የሚሰበስበው የሥጋ ኤክስፖርት መረጃዎች ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከሚሰበሰበው ጋር ሲነጻጸር የቁጥር ልዩነት ሲፈጥር ኢንስቲትዩቱ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንን ሪፖርት በመጠቀም ሪፖርት የሚያዘጋጅ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ተገኝቶ ነበር፡፡

185. ኢንስቲትዩቱ የድጋፍ እና ክትትል ሥራው ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ በነባር፣ ሥራ በጀመሩ እና በግንባታ ላይ ያሉ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሥራ እንቅስቃሴ በመስክ በመከታተልና በየካምፓኒው ደረጃ እንዲጠናቀሩ በማማከር ኢንስቲትዩቱ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የስድስት ወር፣ ዘጠኝ ወር እና ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለከፍተኛ አመራሩ አቅርቦ ማስገምገም አለበት የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

186. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር የኢንዱስትሪዎቹን የሥራ እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችለውን ሪፖርት ከማቀነባበሪያዎቹ በተከታታይ ማግኘት የሚያስችለውን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ለማድረግ ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

187. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

188. ኢንስቲትዩቱ የስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎችን የስራ እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችለውን ሪፖርት በተከታታይ ለማግኘት የሚያስችለውን ስርዓት እንዳልዘረጋ የኢንስቲትዩቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

189. ኢንስቲትዩቱ የስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎችን የምርት መጠን ሪፖርት በተከታታይ ለማግኘት የሚያስችለውን ስርዓት ባለመዘርጋቱ ሪፖርቱን በየሳምንቱ በስልክ እንደሚጠይቅ እና ኢንስቲትዩቱ በየዓመቱ የሚሰበስበው የሥጋ ኤክስፖርት መረጃዎች ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከሚሰበሰበው ጋር ሲነጻጸር የቁጥር ልዩነት ያለው መሆኑ፤

190. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- ኢንስቲትዩቱ የስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎችን የስራ እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችለውን ሪፖርት በተከታታይ ለማግኘት የሚያስችለውን ስርዓት እንዳልዘረጋና የዘርፉ ካምፓኒዎች በጣም ብዙ ስለሆኑና ኢንስቲትዩቱ ያለው የሰው ሀይል አነስተኛ ስለሆነ የዘርፉ የአፈፀፀም ሪፖርት በወቅቱና ወጥ በሆነ መልኩ እንደማይቀበሉና በዳታ ቤዝ ተሞልቶ ስርዓቱ ጠብቆ እንደማይቀበሉ ነገር ግን የካምፓኒዎችን እንቅስቃሴ የሚከታተሉት በሰው ሀይል ስምሪት መሆኑን፣
- ኢንስቲትዩቱ በየዓመቱ የሚሰበስበው የሥጋ ኤክስፖርት መረጃዎች ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከሚሰበሰበው ጋር ሲነጻጸር የቁጥር ልዩነት ሲፈጥር

ኢንስቲትዩቱ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሪፖርት ተአማኒነት ስላለውና ትክክል ስለሆነ እሱን መረጃ ለሪፖርት እንደሚጠቀሙት ገልፀዋል፡፡

191. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሀላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ኢንስቲትዩቱ በዋናነት የተቋቋመዉ የንዑስ ዘርፉ ኢንዱስትሪዎች የሚያመርቱትን ምርት መረጃ በማሰባሰብ ሪፖርት ለማድረግ ሳይሆን ለእነዚህ ተቋማት ዘርፈ ብዙ ድጋፎች ለማድረግ እንደሆነ፤ ነገር ግን የተሰጠዉ ድጋፍም በምርትና ምርታማነታቸዉ ላይ ምን ያህል ዉጤት አምጥቷል የሚለዉን ለመለካት ደግሞ ሪፖርት አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸዋል፤

192. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ሀላፊዎች ለክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ይሁን ይበሉ እንጂ፡-

- በነባር፣ ሥራ በጀመሩ እና በግንባታ ላይ ያሉ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሥራ እንቅስቃሴ በመስክ በመከታተልና በየካምፓኒው ደረጃ እንዲጠናቀሩ በማማከር ኢንስቲትዩቱ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የስድስት ወር፣ ዘጠኝ ወር እና ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለከፍተኛ አመራሩ አቅርቦ ማስገምገም እንዳለበት ስለሚታመን እና ኢንስቲትዩቱ በቅርበት ከኢንደስትሪዎቹ ጋር በመሥራት እንዲሁም ሙያተኞቹን በማሰማራት ሪፖርቱን ማሰባሰብ የሚችል በመሆኑ ከላይ የተገለፀው ሀሳብ ተቀባይነት የለውም፡፡

<u>**በኢንስቲትዩቱ የአማካሪ ምክር ቤት መቋቋሙን በተመለከተ፡-**</u>

193. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

194. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመገምገም፣ ለማማከር እና የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል የአማካሪ ምክር ቤት ሊያቋቁም አለመቻሉ ለኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ተገኝቶ ነበር፡፡

195. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመገምገም፣ ለማማከር እና የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል የአማካሪ ምክር ቤት ሊያቋቁም ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

196. ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሂሳ 3/10/6/5 መጋቢት 25 ቀን 2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መረሃ ግብር የኢንስቲትዩቱን አጠቃላይ የድጋፍ አግባብ እየገመገመ አቅጣጫ የሚሰጥ አማካሪ ቦርድ ማቋቋም እንዲችል የአማካሪ ቦርድ አባል የሚሆኑ ግለሰቦችን ከተለያዩ ዘርፎች የመለየትና የማቋቋም ስራ ለመስራት ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለመተግበር የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ መካተቱን ገልጿል፡፡

197. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

198. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመገምገም፣ ለማማከር እና የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል የአማካሪ ምክር ቤት እንዳልተቋቋመ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

199. የኢኒስቲትዩቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመገምገም፣ ለማማከር እና የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮች ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል የአማካሪ ምክር ቤት ለማቋቋም አቅም ያላቸው ባለሙያዎች ተለይተው ለኢንዱስትሪ ሚንስቴር የተላኩ መሆኑን ገልፀዋል እንዲሁም ለክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ለቁርኝት ድጋፍ ያደርጋሉ የተባሉ የስቲሪንግ ኮሚቴ አባላት ለአማካሪ ምክር ቤትም እንዲሰሩ አቅጣጫ እንደተሰጠ ገልጸዋል፡፡

200. ይሁን እንጂ ይህንን ያስረዳል ተብሎ የቀረበው ማስረጃ ባለሙያዎቹ ተመልምለው ወደ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተልኮ አማካሪ ምክር ቤት እንዲቋቋም/እንዲፀድቅ የተላከ ሳይሆን ከዋና ዳይሬክተሩ ለባለሙያዎቹ የቁርኝት ፕሮግራም ስትሪንግ ኮሚቴ አባል ሆነው ስለመመረጣቸውና የመጀመሪያው የኮሚቴው ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ጥሪ የተላለፈበት በመሆኑ ከላይ የተገለጸው ሀሳብ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

201. ኢንስቲትዩቱ ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር አፈጻጸም ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎች እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

### 3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- ኢንስቲትዩቱ በቅድመ ምርት ሂደትና ድህረ ምርት ሳኒቴሽንና ሀይጅን ላይ በስንቅነሽ ዶሮ እርባታ እና ዶሮ ስጋ ማቀነባበሪያ ድርጅት በመገኘት የዶሮ ስጋ ምርት በጥራት እንዲመረት ሙያዊ ድጋፍ ያደረገ መሆኑ፤
- ለመኖ ማቀነባበሪያዎች ጥራቱን የጠበቀና ገበያ ተኮር የእንስሳት መኖ እንዲያመርቱ በተሰጣቸው የምክር አገልግሎት 7 መኖ ማቀነባበሪያዎችና 13 ዩኒኖች 8,753.25 ኩንታል መኖ ለማቀነባበር አቅደው 13,087.18 ኩንታል አቀነባብረው ለገበያ ያቀረቡ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ በ2010 ዓ.ም 860 የወተት ናሙና ወስዶ ኬሚካላዊና ማይክሮ ባዮሎጂካል ፍተሻ ያደረገ መሆኑ፤
- በኦዲቱ ወቅት የታዩ ኤክስፖርት ቄራዎች እንስሳቶች ለረጅም ሰአት ተጉዘው ማረፊያ ሊሆናቸው የሚችል ቦታ(holding areas) እና በቂ የውሃ መጠጫ ገንዳዎች ያዘጋጁ መሆኑ፤
- በኦዲቱ ወቅት የታዩ የወተትና ስጋ ማቀነባበሪያዎች ላብራቶሪ ያላቸው መሆኑ
- ኢንስቲትዩቱ ከስጋ ማቀነባበሪያዎቹ ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሙ፤
- ኢንስቲትዩቱ በስጋ ኤክስፖርት ዙሪያ በሌሎች ሀገራት ያለውን አማራጭ መዳረሻ ገበያዎችን በራሱና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ገበያ ማፈላለጉ

- ኢንስቲትዩቱ ሌሎች አካላት ባዘጋጁት ባዛር ቄራዎች እንዲሳተፉና ምርታቸውን እንዲያስተዋውቁ ማድረጉ፤
- ኢንስቲትዩቱ በ2009 ዓ.ም እና በ2010 ዓ.ም ኢንስቲትዩቱ ለስጋ ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንት የሚያስፈልጉ የቁም እንስሳት አቅርቦት ላይ የደሰሳ ጥናት ማድረጉ
- ኢንስቲትዩቱ ለሁለት ኤክስፖርት ቄራዎች (አቢሲኒያና አክሽከር) እንስሳት ከሚያቀርቡ ማህበራት ጋር ያስተሳሰረ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ በ2010 በጀት ዓመት መጨረሻ ሰኔ ወር ላይ አርሲ ዩኒቨርሲቲ ከሉና ቄራ፣ አክሽከር ቄራ፣ ሀላል ቄራ፣ኦርጋኒክ ቄራ፣አለና ቄራ፣ በቆጂ ትኩስ ወተትና አዲስ አለም ሞጆ የመኖ ማቀነባበሪያ ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሙ፤
- ኢንስቲትዩቱ የስጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችል የፕሮጀክት ፕሮፋይል ማዘጋጀቱ፤
- ኢንስቲትዩቱ የወተትና ወተት ውጤቶች ኤክስፖርት እቅድ ማዘጋጀቱ ፤
- በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ ስልጠናዎች በእቅድ የተያዙ መሆናቸው፤ ኢንስቲትዩቱ ከአዲስ አበባና ደ/ዘይት አነሰተኛ ኢንተርፕራዝ ለመጡ 5 ወንድና 2 ሴት በድምሩ ለ7 ሰልጣኞች በእርጎ አዘገጃጀት እና በቺዝ አሰራር ላይ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና መስጠቱ፤
- ኢንስቲትዩቱ የስጋ ኤክስፖርት ቄራዎችን ጥራቱን የጠበቀና በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ለማምረት እንዲችሉ ከአየር ላንድ ሀገር በዘርፉ ልምድ ያለው ባለሙያ በማስመጣት ሁሉም ቄራዎች ያለባቸውን ክፍተትና የስልጠና ፍላጎት በመዳሰስ በቄራ ጽዳትና ንጽህና፣ የምግብ ደህንነት፣ HACCP (Hazard Analysis and Critical Control Point)፣ የስጋ አቆራረጥና አበላለት ዙሪያ በሞጆ ክላስተር፣ በአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት፣ በአበርገሌ ቄራ፣ በጅግጅጋ እና ደ/ዘይት ክላስተሮች ለ134 ሰልጣኞች ለግማሽ ቀን የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና የተሰጠ መሆኑ፤

- በኤክስፖርት ቄራዎች የሀላል ስርዓትን ተከትሎ የእንስሳት እርድ በማካሄድ ደንበኞችን ለማርካት ከሳውዲአረቢያ በመጣ አንድ ባለሙያ ለ12 ተከታታይ ቀናት ለ34 ወንድና 1 ሴት በድምሩ ለ35 ሰልጣኞች በኦሮሚያ እስልምና ጉዳዮች፣ በስጋ ላኪዎች ማህበርና በኢንስቲትዩቱ የጋራ ትብብር በአዲስ አበባ ከተማ ስልጠና የተሰጠ መሆኑ፤
- ኢንስቲትዩቱ የስጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎችን የምርት መጠን በየሳምንቱ በስልክ የሚቀበል መሆኑ፤

## 3.2 <u>እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው</u>

- በናሙና ተመርጠው በታዩ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች ኢንስቲትዩቱ በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት በመስጠት ውጤት ማስመዝገብ አለመቻሉ፣
- ወተትና የወተት ውጤቶች የጥራት ደረጃ አጠባበቅ ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል ክትትል አለመድረጉ እና ከወተት ማቀነባበሪያዎች የምርት ናሙና በማሰባሰብ የመጀመሪያ ደረጃ፣ ኬሚካላዊና ማይክሮባዮሎጂካዊ ጥራት ፍተሻ በማድረግ ማቀነባበሪያዎቹ እንዲያሻሽሉ ድጋፍ አለመሰጠቱ፤
- በመኖ ምርቶች ላይ የላብራቶሪ ትንተና እንዲደረግባቸው ኢንስቲትዩቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት አለመሥራቱ፣
- በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ በምርት ሂደት ባለሙያዎቹ ቀርበው እገዛ ያላደረጉ ሲሆን ባለሙያዎቹ ወደ ኢንዱስትሪዎቹ በሚሄደበት ወቅት ስለ ምርት ሂደቱ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በጥያቄ ስለሚያባክኑ ማቀነባበሪያዎቹ ለኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ያላቸው ሙያዊ አመለካከት በመቀየሩ ሙያተኞቹን ለማስተናገድ አለመቻላቸው እና በምርት ዕቅድ ላይ አብሮ አለማቀድ እና የኢንስቲትዩቱ ድርሻ ምን እንደሆነ በዕቅዳቸው ላይ የማይገለጽ እና የማይታወቅ መሆኑ፣

- ከጥራት ጋር በተያያዘ የሥጋ እና ወተት ላብራቶሪዎች የተለየ ክፍል የሌላቸው፣ ያረጁና ጥገና ያልተደረገላቸው እና በትክክል ስለመስራታቸው ማረጋገጫ (Calibration test) ያልተደረጉ መሆኑ፣ በቂ የላብራቶሪ ፋሲሊቲ (ይህም፡-የተለየ የላብራቶሪ ክፍል፣ ኤር ኮንዲሽነር፣ ፋኖች እና ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች...)፣ የላብራቶሪ ማስኬጃ መመሪያ ወይም ማንዋል የሌላቸው፣ የላብራቶሪ ቆሻሻ መቆጣጠሪያ (residue monitoring) መሳሪያ አለመኖር እና ኢንስቲትዩቱም ሞዴል ሰርቶ ማሳያዎች እና ላብራቶሪዎችን በማቋቋም በዚሁ መሰረት እንዲስፋፉ አለማድረጉ፣

- የወተት ማቀነባበሪያዎቹ የሰለጠነ የላብራቶሪ ባለሙያ እና መሳሪያዎች የሌላቸው በመሆኑ የማይክሮባይሎጂካል፣ አፍሊቶክሲን እና ኬሚካል አናሊስስ የማያከናውኑ እና አቅራቢዎች ለወተት ባልተዘጋጀ እና ንጽህና በሌለው ዕቃ የሚያቀርቡ፣ ማቀነባበሪያዎቹ እና አቅራቢዎች ለወተት ሥራ በተዘጋጀ ተሽከርካሪ ሌሎች ዕቃዎችን የሚያጓጉዙ መሆኑ፣ ወተት ከረጅም ርቀት በማጓጓዝ የሚመጣበት ሁኔታ መኖሩ እና የተለየ እና ንጽህናውን የጠበቀ የወተት መረከቢያና መሸጫ ቦታዎች የሌላቸው መሆኑ እንዲሁም የወተት ማቀነባበሪያዎች የወተት ማሰባሰቢያና ማቀዝቀዣ ማዕከል እንዲያቋቁሙ ድጋፍ አለመደረጉ፤

- በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ኢንስቲትዩቱ በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ድጋፍ የማያደርግላቸው መሆኑ፣

- የሥጋ ኢንዱስትሪዎች የዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟላ ምርቶች ለሃገር ውስጥና ለአለም ገበያ በስፋት ማቅረብ አለመቻላቸው፤ የሥጋ ኢንዱስትሪዎች አፈጻጸም ከዓመት ዓመት እየቀነሰ የሚሄድበት ሁኔታ መስተዋሉ ለዘርፉ ስጋት መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ያለ ችግሮችን በመለየት ሊለሙ የሚችሉ ወጪ ቆጣቢ፣ ምርትና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ እና የምርት ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና

ሥርጸት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች እንዲሸጋገር በማድረግ ኢንዱስትሪዎቹም የራሳቸውን የምርምርና ሥርጸት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ ሊደግፍ አለመቻሉ፣

- ስጋን በገፈፋ (carcass) መልክ ከመላክ ይልቅ በተቆራረጠ መልኩ ሊልክ የሚችልበትን የማቀነባበር ሥርዓት አለመዘርጋት ፣ ከደጋውና ወይናደጋው የሀገሪቱ ክፍል ለኤክስፖርት ቄራዎች የሚቀርቡት እንስሳት ሥጋ ቶሎ የመጥቆር ባህሪ ያለው በመሆኑ የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች የቆላ ሥጋን ብቻ ለኤክስፖርት መጠቀማቸው ለዘርፉ ከፍተኛ ሥጋት ሆኖ እያለ በምርምር መፍትሄ መስጠት አለመቻሉ እንዲሁም ጠንካራ ሥጋን ማለስለስ የሚችል ቴክኖሎጂዎች ቢኖሩም ይህን ለመተግበር የሚያስችል ቴክኖሎጂና ሥልት ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ፣
- ወተትና ወተት ውጤቶች ጥራትና ቁጥጥር እንዲሁም ደህንነት ማረጋገጫ ላይ ምርምር ማካሄድ አለመቻሉ ፣ በፍየል ወተት ላይ ጥናት አለመደረጉ እንዲሁም በኬሚካል ወተትን የማቆየቱ ሂደት ጠቀሜታውና ጉዳቱ ተለይቶ ለማቀነባበሪያዎቹ ሳይንሳዊ የሆነ ጥናት እንዲሰጣቸው አለመደረጉ፣
- የሥጋ፣ የወተት እና የመኖ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ታዳሽ የኃይል ምንጮችን የማይጠቀሙ እና የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ያልተሸፈኑና (Safety tank) የሌላቸው መሆኑ፣
- ለኢንዱስትሪዎች ከፍተኛ ችግር ሆኖ የሚታየውን የመብራት መቆራረጥ በተወሰነ ደረጃ ማቃለል የሚችለውን ባዮጋዝ በናሙና ተመርጠው በታዩ ኢንዱስትሪዎች ላይ እንዲገነቡ እገዛ አለማድረጉ፤ ይህም አልሚ ትኩስ ወተት ማቀነባበሪያ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ እና ውሃን መልሶ አጣርቶ ለመጠቀም የሚያስችል ቴክኖሎጂን ለመጠቀም በዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ የሚያደርግለት እገዛ የሌለ መሆኑ፣

- የሥጋ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ወቅታዊ የቴክኒክ ፍተሻ የሚያካሂዱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ዕቅድ ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞችን...) ባካተተ መልኩ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት አፈጻጸሙን ያካተተ ሪፖርት ማግኘት አለመቻሉ፣
- ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ምርቶችን ለመተካት የሚያስችሉ ምርቶችን በሃገር ውስጥ በጥራትና በብዛት እንዲመረቱ የሚያስችል ስልት ኢንስቲትዩቱ ቀይሶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- በወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን በኤክስፖርትና ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባውን ወተት ለመተካት በሚያስችል (Import substitution) ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ እንዲችሉ አለመደረጉ፣
- የወተትና ወተት ውጤቶች ኤክስፖርት ዕቅድ አለመያዙ ለዘርፉ ትኩረት አለመሰጠቱን፣
- የሀገራችን የሥጋ ማቀነባበሪያዎች በተወሰኑ አይነት (በፍየል እና በግ) ሥጋ ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን በሌሎች የተቀነባበረ የፍየል፣ በግ፣ ዳልጋ ከብት እና ግመል ወ.ዘ.ተ ሥጋ ላይ ትኩረት አድርገው የማይሠሩ መሆኑን እንዲሁም በሙሉ አቅማቸው እንዳይሰሩ ለእርድ የሚቀርቡ እንስሳት ኤክስፖርት ቄራዎች በሚፈልጉት ዓይነት፣ ዕድሜ፣ ክብደትና ዋጋ እንዲቀርብ ክትትል አለመደረጉ፤ እንዲሁም ብዛትን አስመልክቶ የሥጋ እና ወተት ማቀነባበሪያዎቹ የማምረት አቅም ያላቸው ቢሆንም በሙሉ አቅማቸው እያመረቱ አለመሆኑ፣
- የሀገራችን የወተት ማቀነባበሪያዎች በተወሰኑ አይነት (ፓስቸራይዝድ ወተት፣ እርጎ፣ አይብ፣ የገበታ ቅቤ እና የምግብ ቅቤ) ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን በሌሎች ክሬም፣ የተፈጨ ቺዝ፣ ፕሮቫለን ቺዝ፣

ሞዞሬላ ቺዝ፣ ፌታ ቺዝ፣ እስሞክድ ቺዝ፣ ፎንቲና ቺዝ ወ.ዘ.ተ ላይ ትኩረት እድርገው የማይሠሩ መሆኑ፣

- በወተት እና ሥጋ ምርቶች ላይ የሚካሄዱ የንግድ ትርኢቶችና ባዛሮች በጥናት ላይ ያልተመረኮዙ እና ሁሉንም የወተት እና ሥጋ ማቀነባበሪያዎች ያላሳተፉ እንዲሁም ውጤታቸው የማይለካ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ኢንዱስትሪዎቹን ከጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች እና ከውጭ ሃገር ገዥዎች ጋር በዘመናዊ የግብይት ሥርዓት የማስተሳሰር ሥራ ሊያከናውን አለመቻሉ፣
- ለኤክስፖርት ቄራዎች እንስሳት የሚያቀርቡ ማህበራትና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችና ነጋዴዎችን በመለየት ከቄራዎች ጋር ማስተሳሰር አለመቻሉ፣ አሁን ያለው የሥጋ ኤክስፖርት ገበያ በደንበኞች ትዕዛዝ እና ቄራዎች በራሳቸው መንገድ ገበያን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት ላይ ብቻ የተንጠለጠለ እንጂ ኢንስቲትዩቱ በሌሎች ሀገራት ያለውን አማራጭ መዳረሻ ገበያዎችን በራሱና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር እና ኢምባሲዎች) ጋር በመሆን ገበያ ማፈላለግ አለመቻሉ፣
- በበረዶ የቀዘቀዘ የዳልጋ ከብት ሥጋን መግዛት ወደ ሚፈልጉ ሀገሮች አንጎላ፣ ግብጽ፣ ቻይና፣ ኢራን፣ አልጄሪያና ሞሮኮ ገበያዎች መግባት አለመቻሉ፤ በገዥ ሀገራት በሚደረጉ የምርት ማስተዋወቂያ መድረኮች ላይ የእንስሳት ምርት ላኪዎች ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ የሚጋብዝ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ እና የሥጋ መዳረሻ ገበያዎችን የሥጋ ፍላጎት፣ ዋጋና የተወዳዳሪ ሀገራት የምርት አቅርቦት ዙሪያ የደሰሳ ጥናቶችን በማከናወን መረጃዎችን በማጠናቀር ቄራዎች እንዲደርሳቸው አለማድረጉ፣
- የወተት አቅርቦት ችግር እና በጾም ወቅት የሚፈጠረው የገበያ እጥረት ከፍተኛ በመሆኑ ባለሃብቱ በሥራው እምነት እንዲያጣ እያደረገ መሆኑ እንዲሁም ሱማሌ እና ጅቡቲ አከባቢ ከፍተኛ የወተት ፍላጎት ያለ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ የአከባቢዎቹን ፍላጎት በመለየት

ማቀነባበሪያዎቹን ሊደግፍ አለመቻሉ እንዲሁም የወተት ዘርፉ የወጪ ምርቶች የገበያ እስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ፣ በተለይ በአዳማ አከባቢ የሚገኘው ያቅላ ወተት ማቀነባበሪያ ከገበያ ለመውጣት የተገደደ መሆኑ፣

- ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን አቅርቦት እጥረት መንስኤዎች በመለየት በአቅርቦት ዘርፍ ከተሰማሩ ባለሃብቶችና ተቋማት ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችል ደሰሳ ጥናት (Supply chain) በማካሄድ ተግባራዊ እንዲሆን አለመደረጉ፣
- የማሽኒያ፣ የኬሚካል፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎች፣ የቁም እንስሳት አቅርቦት በተለይ በሥጋና ወተት ፍላጎትና እንስሳት አቅርቦት ላይ ደሰሳ ጥናት በማከናወን ለማቀነባበሪያዎቹ አለመሰራጨቱና ተግባራዊ አለመደረጉ፤ በተጨማሪም የእንስሳት አቅርቦትን ችግር ለመፍታት የግል ባለሃብቶችና የቄራ ባለቤቶች መሬት ወስደው የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል እንዲያረቡ እና እንዲያደልቡ ብሎም ከይዞታቸው ለእርድ እንዲያቀርቡ የእንስሳት እርባታ (ራንች) እንዲያቋቁሙ አለመደረጉ፣
- ለመኖ ማቀነባበሪያ ግብዓትነት የሚያገለግሉ የፋብሪካ ተረፈ ምርቶች ለተደጋጋሚ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተጋለጡ በመሆናቸው የዋጋ ጭማሪ እየተስተዋለባቸው መሆኑ እንዲሁም ማቀነባበሪያዎቹ በቂ ገበያ ያለማግኘት እና ለሥራው የሚያስፈልግ የሰው ኃይል ከማሟላት ይልቅ በተወሰነ ባለሙያዎች ብቻ ሥራን የሚያከናውኑ መሆኑ፣
- የዳበረ ልምድ ካላቸው ሀገራት በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም እና በሥጋ ሎጂስቲክ አመራር ላይ ኢንስቲትዩቱ ለ ኢንዱስትሪዎቹ ድጋፍ ማድረግ አለመቻሉ፣
- ኢንስቲትዩቱ በኢንዱስትሪዎቹ ለሚከሰተው የመሣሪያዎች ብልሽትና የመለዋወጫዎች ችግር አስመልክቶ የሥልጠና እና ድጋፍ አገልግሎት አለመስጠቱ እንዲሁም ከኢንስቲትዩቱ ለሥራ ተልከው ወደ ኢንዱስትሪዎቹ የሚሄዱ ባለሙያዎች በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም ላይ እገዛ ለማድረግ የሚያስችል በቂ

የተግባር ክህሎት የሌላቸው መሆኑ እና ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ውጤቶች በመዳረሻ ሀገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን በመለየት ለኢንዱስትሪዎቹ ያላስተዋወቀ እና ማስረጃውን ያልሰጣቸው/ያላሰራጨ መሆኑ፣

- በኢንስቲትዩቱ የተለያዩ ንብረቶች ውሳኔ ያላገኙ እና ጥቅም ላይ የማይውሉ፣ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች እና የእርሻ መሳሪያዎች ውሳኔ ያገኙ ነገር ግን ያልተወገደ እንዲሁም የተለያዩ ንብረቶች/መሣሪያዎች ያረጁና የተበላሹ መሆኑ ፣ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውና ጥቅም ላይ የማይውሉ ኬሚካሎችና የወተት ላብራቶሪ መሳሪያዎች መኖራቸውን፣
- በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎች ያልተዘጋጁና ያልተሰራጩ እንዲሁም ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሃብቶች ጠቋሚ ጥናት በማድረግ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል በማድረግ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ሊሰጥ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ እና በአፈጻጸም ወቅት ለተከሰቱ ችግሮች ስለተሰጠው የማስተካከያ እርምጃ የሚያመለክት ማስረጃ በናሙና በታዩት ማቀነባበሪያዎች ተጠይቆ ማግኘት አለመቻሉ፣
- ኢንቨስትመንቱ እንዳይስፋፋ እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮች በአፋጣኝ መፍትሄ የማይሰጣቸው መሆኑ፤ እንዲሁም ከማስፋፋት ጋር በተያያዘ የራሳቸው እንስሳት ማቆያና ማደለቢያ እንዲኖራቸው የሚጠይቁትን መሬት የማያገኙ መሆኑ እና በልማት ባንክ በኩል ለዘርፉ ትኩረት ባለመስጠት የሚሰጣቸው ብድር የሚጓተትበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሃገራትና ካምፓኒዎችን ለይቶ ተሞክሮዎቹን አቀናብሮ ለማቀነባበሪያዎቹ በማሰራጨት ተግባራዊነቱን የማይከታተል መሆኑ፣

- በኢንስቲትዩቱ የተቀናበሩና የተሰራጩ መልካም ተሞክሮ ሰነዶች ኢንዱስትሪዎቹ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው ማቅረብ አለመቻላቸው እና የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎችም ወደ ውጪ ሃገር ሄደው ከመጡ በኋላ ለማቀነባበሪያዎቹ ስላዩአቸው ተሞክሮዎች ያገኙትን ልምድ የማያካፍሏቸው መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያና ሌሎች መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን እና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጩ ሊያደርግ አለመቻሉ፤ ይህም ኢንስቲትዩቱ የውጭ ገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብ በመተንተን እና አደራጅቶ በመያዝ ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት እና የወጪ ምርቶች የገበያ እስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ፣

- ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የሚውሉ የኢንቨስትመንት ቦታዎችን በዝርዝር ለይቶ እንዲታወቁ በማድረግ መረጃውን በዳታ ቤዝ በማጠናቀር ለባለሃብቶች በቀላሉ መስጠት አለመቻሉ፣

- ኢንስቲትዩቱ በሀገሪቱ የሚገኙትን የክልሎች የወተት ሃብት (Milk Shed)ና የመኖ የማምረት አቅም እንዲሁም የእንስሳት አቅርቦት መጠን በመለየት መረጃዎችን ማደራጀት አለመቻሉ

- የእንስሳት ዱካን (Tracibility) ለመመዝገብ የሚያስችል መዝገብ (records) ተግባራዊ እንዲደረግ በማድረግ ከግበርነ ሚ/ር ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን በማጎልበት የእንስሳት ጤና ሥርዓትና ቁጥጥርን አስመልክቶ መረጃዎችን ለተቀባይ ሀገራት የማድረስና የማስተዋወቅ ሥራ አለመከናወኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ ከክልሎችና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየት ወደ ሥራ እንዲገቡ ሊያደርግ አለመቻሉ፣

- ኢንስቲትዩቱ በተለይም በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር ውጤታማ የምርት የቴክኖሎጂና የሥልጠና ትስስር እንዲኖራቸው በማድረግ ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ማድረስ አለመቻሉ፤ እንዲሁም የህብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው አቅማቸውን በማሳደግ የእርድ እንስሳት እና ወተት እንዲያቀርቡ በየደረጃው ካለው ህብረት ሥራ ማህበራት አደራጅ መ/ቤቶች ጋር በጋራ እንዲሰራ አለመደረጉ፣

- በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በእቅዱ መሰረት ተፈጻሚ አለመሆኑ፣ ተግባር ተኮርና ወቅቱን የጠበቀ አለመሆኑ፤ ይህም ሥልጠናው የሥጋ እና የወተት ገበያ በቀዘቀዘ ወቅት (ሥጋ ወደ አረብ ሀገራት የሚላክ በመሆኑ ከሙስሊም በዓላት ውጪ እና ወተት በሀገር ውስጥ የሚሸጥ በመሆኑ በጾም ወቅት) ላይ ብቻ የማይሰጥ በመሆኑ ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከታቸውን ባለሙያ ለመላክ የሚገደዱ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ የትምህርት፣ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስር ፎረም ያቋቋመ ቢሆንም በቀጣይነት ለመተግበር የሚያስችለው መመሪያ ወይም ማንዋል አዘጋጅቶ ወደ ሥራ ሊገባ አለመቻሉ፤ ይህም በዘርፉ የአገር ውስጥ ምርምር አቅም እንዲጠናከር እና የዘርፉን የዝቅተኛና መካከለኛ የሰው ኃይል ፍላጎትን ለማሟላት በኢንዱስትሪዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ጋር በጋራ የተከናወኑ ተግባራት አለመኖሩ፣ እንዲሁም የትስስር ፎረሙ ለማቀነባበሪያዎቹ ያለው ጠቀሜታ አነስተኛ መሆኑ እና የወደፊት ጠቀሜታውን ባለመረዳታቸው ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስቸግር መሆኑን፣

- ኢንስቲትዩቱ የኢንዱስትሪዎቹን የሥራ እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችለውን ሪፖርት ከማቀነባበሪያዎቹ በተከታታይ ማግኘት የሚያስችለውን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፤ ይህም፡- ኢንስቲትዩቱ በየዓመቱ የሚሰበስበው የኤክስፖርት መረጃዎች

ከገቢዎችና ጉምሩክ ከሚሰበሰበው ጋር ሲነጻጸር የቁጥር ልዩነት ሊፈጥር መቻሉ፣

- ኢንስቲትዩቱ የሚሰጠውን ድጋፍ ተደራሽ ለማድረግ በክልሎች የራሱ መዋቅር በተዋረድ የሌለው ቢሆንም በኢንዱስትሪዎቹ አከባቢ ከሚገኙ እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው በከተማ መስተዳደር የንግድና ኢንዱስትሪ የሥራ ሂደቶች፣ የኢንቨስትመንት ቢሮዎች እና ከእንስሳት ሃብት ልማት ኤጀንሲዎች ጋር በቅንጅት አለመስራቱ፣
- ኢንስቲትዩቱ በወጪ ንግድ ሂደት ውስጥ የሚታዩ ማነቆዎችን ለመፍታት ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር፣ ከባንኮች፣ ከጉምሩክ፣ ከአየር መንገድ፣ ከግብርና ሚ/ር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት እና ለመከታተል እንዲሁም ችግር ሲገጥም መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል መድረክ/ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የኮልድ ቼይን ሰንሰለት ውስጥ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ከቄራዎች፣ ከአየር መንገድ፣ ከኤርፖርቶች ድርጅትና ከትራንስፖርት ሚ/ር ጋር ቅንጅታዊ አሰራሮችን በመዘርጋት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሞ በሰነዱ መሰረት ወደ ተግባር ሊገባ አለመቻሉ፣
- በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመገምገም፣ ለማማከር እና የአቅም ግንባታ መርሀ ግብሮች ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል የአማካሪ ምክር ቤት ሊቋቋም አለመቻሉ፣

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

202. በመጀመሪያው የክዋኔ ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑት የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡

203. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ባልተስተካከሉና የእርምት እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡